# ፍሬ አልባ በለሶች
## (የቆብ ውስጥ ገመና)

**በሚሌኒዮሙ መጨረሻ**
**የምንኩስና ማስታወሻ**

ከተገኝ ብልሐቱ

ሰኔ, 1999 ዓ.ም

ከሀገር ውጪ ለመውጣት
ለእውነተኛ የምንኩስና ዓለማ
የነአባ ዓለም በዘዴ አለባበስ

ምዕራፍ 6 በምንኩስና ስም እየተፈጸሙ ያሉ ውንብድናዎች ......... 34
ከምንኩስና ወደ እስልምና
ከምንኩስና ወደ እስልምና ከእስልምና ወደ ምንኩስና
ሆቴል ውስጥ ከሴተኛ አዳሪ ጋር ተደባድቦ የተባረረው የደብር አለቃ

ምዕራፍ 7 ጵጵስናና መስፈርቱ በመጽሐፍ ቅዱስ .......................... 41
የጳጳስ የሹመት መስፈርት በፍትሐ ነገሥት
በጵጵስና ማዕርግ የተፈጸመ የግድያ ወንጀል
ከቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጠ መግለጫ
ምንኩስናን ለማስፋፋት እየተፈጸሙ ያሉ ሴራዎች
የስልጣን የበላይነትን በመቆጣጠር
ባማሩ ሕንፃዎች መነኮሳት ብቻ እንዲቀድሱ ማድረግ
ወደ ውጪ ሀገር መላክ
የትምህርት ዕድል ቅድሚያ መስጠት
ምንኩስና አስመልክቶ የደራሲው ዓላማና ራዕይ
ገዳማዊ አደረጃጀት
የአመክሮና የትምህርት ገዳም
የምናኔ ገዳም
ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የቀረበ ጥያቄ



# መግቢያ

ብዙ ሰዎች የቤተክርስቲያን አባቶች ለምን ይዘለፋሉ ይላሉ እንደ አባትነታቸው የአባትነት ስራ ሰርተው ቢገኙ እንደተባለውም ሊዘለፉ አይገባም እንዲያውም ሊከበሩ እንጂ በአባትነት ቦታ ተቀምጠው የአባትነት ስራ ሳይሆን በአባትነት ስም የወንበዴ ስራ ሲሰሩ ሲገኙ ዝም ማለት ግን ቤተክርስቲያን የወንበዴዎች ዋሻ እንድትሆን ምዕመናንም በወንበዴዎች ትምህርት እንዲወሰዱ ማድረግ ነው ወንበዴዎችን ማጋለጥና ስራቸውን ለምዕመናን ማሳወቅ ደግሞ ምዕመናን ከክፋ ስራቸው እንዲጠነቀቁ ያደርጋል::
ይህም ጌታችን ያደረገው ነው በማቴዎስ ወንጌል በሙሴ ወንበር ላይ የተቀመጡትን ጻሐፍትና ፈሪሳውያንን እነርሱን «እናንተ እውሮችና ደንቆሮዎች» እያለ አይነ ልቡናቸው መታወሩንና እዝነ ልቡናቸው መደንቆሩን ነግሮ የውንብድናና የማታለል ስራቸውን ዘርዝሮ ነግሮአቸዋል ለሕዝብም አሳውቋል:: ማቴ 23:1-36

በሉቃስ ወንጌልም ሕዝቡ ሁሉ ሲሰሙ ደቀመዛሙርቱን «ረጅም ልብስ ለብሰው መዞር ከሚፈልጉ በገበያ ሰላምታ በምኩራብም የከበሬታ ወንበር በምሳም የከበሬታ ስፍራ ከሚወዱ ጻፎች ተጠበቁ የመበለቶችን ቤት የሚበሉ ፀሎታቸውንም በማስረዘም የሚያመካኙ እነዚህ የባሰ ፍርድ ይቀበላሉ::» ብሎ በሕዝቡ ፊት ደቀመዛሙርቱ ከወንበዴዎች ስራ እንዲጠነቀቁ ተናሮአል:: ሉቃ 20:45-47

ሐዋርያው ጳውሎስም በወቅቱ ያታልሉ የነበሩ የአይሁድ መምህራንን ክፉ ስራቸውን አጋልጧል ሮሜ 2:1-9 እኔም ከዚህ የተለየ አይደለም ያደረግሁት ጌታችን በሙሴ ወንበር (ሕገ ኦሪት) ተቀምጠው ሲያወናብዱና ሲያታልሉ የነበሩትን እንዳጋለጠና ለሕዝቡ እንዳስጠነቀቀ እኔም በቤተክርስቲያን ውስጥ በምንኩስና ስም የሚያወናብዱትን አጋልጫለሁ::

ከብዙ በጥቂቱ በዚች መጽሐፍ ውስጥ የተገለጠው ስራቸውን አንብቦ አሁንም ለምን ተጋለጡ የሚል ካለ ፍርዱን ለአንባቢ እተወዋለሁ ከላይ ባየናቸው ምዕራፎች ጌታችንም ሆነ ሐዋርው ጳውሎስ በወቅቱ ምኩራቡን ይመሩ የነበሩትን የቡድን ስም በመጥራት እንጅ የግለሰብ ስም በመጥራት አልዘለፉም እኔም ይህን ወንጌላዊ ትምህርት መሠረት በማድረግ የምንኩስና ሥርዓት የሌቦችና የወንበዴዎች መጠለያ መሆኑን በትምህርትና በማስረጃ አስደግፌ ከማሳየት በስተቀር የግለሰብ ስም አባ እገሌ ብየ ስም አልጠራሁም::

ለቤተክርስቲያን የሚጠቅማት መስሎም አልታየኝም የግለሰቦችን ስም መጥራትና በግል ማጋለጥ ቢያስፈልግ ኑሮ ከጳጳስ እስከተራ መነኩሴ የሚያጋልጡ በፎቶግራፍና በሌሎችም ማስረጃዎች የተደገፉ ለማየትና ለመስማት የሚዘገንኑ ድርጊቶች አግኝቼ ነበር ነገር ግን እኔ ስርዓቱ መበላሸቱን ማሳየትና እንዲስተካከል ለመጠቆም እንጂ ጉዳዩ ከግለሰቦቹ ጋር ስላልሆነና ከግል ጥላቻ ተነስቶ መጻፍም ከክርስትና አንፃር ተገቢ ስላልሆነ ደግሞም ግለሰቦቹን ያበላሻቸው የስርዓቱ መበላሸትና ቁጥጥር አለመኖር ስለሆነ የግለሰቦቹን ሞራል ሊነካ የሚችለውን እየመረጥሁ በመተው የስርዓቱን መበላሸት ያሳያሉ ያልኋቸውን ብቻ በማካተት ጽፌአለሁ::

በእርግጥ አንዳንዶቹ ማስረጃዎች የማይታለፉ ስለሆኑና ማስረጃዎች ራሳቸው የሚያጋልጡ ስለሆነ የተጠነቀቅሁትን ያህል አልሆኑልኝም ያም ሆኖ ስራቸው እራሱ አጋለጣቸው እንጂ እኔ ስም አልጠራሁም ሌላው ቀርቶ በሌላ ቦታ ሲያታልሉ የማውቃቸውና በአዲስ አበባም በፒያሳ በአራት ኪሎና በካሳንችስ ጭፈራ ቤቶች አድረው ጠዋት ቤተ ክርስቲያን ገብተው የሚቀድሱ የደብር አስተዳዳሪዎችና ቀዳሾችን በፎቶግራፍ የተደገፈ ድርጊታቸውን ስለማንነታቸው የሚያሳይ ማስረጃ ቢኖረኝም ድርጊታቸውን ከመግለፅ በስተቀር ስማቸውንና የሚቀድሱበትን ቤተ ክርስቲያን አልጠራሁም ፎቶግራፋቸውንም አላወጣሁም ይህም የግለሰቦችን ስም መጥራትና የግል ኃጢአታቸውን መዘርዘሩ ጠቃሚ መስሎ ስላታየኝ ነው የቤተ ክርስቲያኗ ችግር የማይፈታ ከሆነና ስርዓቱ የማይስተካከል ከሆነ እንዳስፈላጊነቱ እግዚአብሔር ቢፈቅድ ወደ ፊት ይሆናል::

ይህንንም ለመጻፍ የተገደድሁት በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚታዩ ችግሮች እንዲስተካከሉ በማደርገው ጩኸት ጩኸቴን ሰምቶ ችግሩን ከማስተካከል ይልቅ ጩኸቴን ለማፈን እኔን ማሳደዱ እንደ መፍትሔ በመውሰዱ ሕዝቡ የጩኸቴን ድምጽ ሰምቶ ችግሩን ተረድቶ የራሱን አስተዋጽኦ ያደርግ ዘንድ ነው ከዚህ ውጪ ከግለሰቦቹ የግል ጥላቻ ኖሮኝ ወይም በዚህ ክብር አገኛለሁ ብዬ አይደለም አማራጭ ባጣ ነው እንጂ ወይም የቤተክርስቲያኔ ዓፍረት የኔ ሀፍረት ሳይሆን ቀርቶ አይደለም::



# ምዕራፍ አንድ

# ጋብቻና ድንግልና በመጽሐፍ ቅዱስ

## እግዚአብሔርን ለማገልገል ማግባትና አለማግባት

እግዚአብሔርን ብዙዎች ከጋብቻ ርቀው ያገለገሉትን ያህል በጋብቻ ተወስነው ያገለገሉትም ያንኑ ያህል ብዙዎች ናቸው በብሉይ ኪዳን እነመልከ ጼዴቅ እነ ኤርምያስ እነ ኤልያስ በድንግልና አገልግለውታል:: /ኤር 16÷1/ በትዳር ተወስነው ደግሞ እነ ሙሴ፣እነ አሮን፣እነ ኢሳይያስ አገልግለውታል /ዘዳ 2÷21፣ዘኍ 12÷1፣ዘዳ 6÷23፣ኢሳ 8÷3/

በአዲስ ኪዳንም  እነ ዮሐንስ መጥምቅ እነ ሐዋርያው ጳውሎስ በድንግልና እንዳገለገሉት ሁሉ ጴጥሮስና ሌሎችም ሐዋርያት ሚስታቸውን ይዘው እየዞሩ አገልግለውታል 1ኛ ቆሮ 9፡3 ::

የእግዚአብሔር ጥሪ በማግባትና ባለማግባት ላይ የተመሠረተ አይደለም በራሱ ምርጫና በተጠሪው ፈቃድ ላይ እንጂ ማንንም አንተ ያገባህ ነህ አንተ ያላገባህ ነህ ብሎ ጠርቶ አያውቅም:: ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር በድንግልና ለሚኖሩት ብቻ የሚያደላና ጸጋውም በይበልጥ በነርሱ ላይ የሚገለጥ እንደሆነ አድርገው የሚያስቡ አሉ::

በእርግጥ ከጋብቻ ርቆ ማገልገል አገልግሎትን የተቀላጠፈ ለማድረግ በጋብቻ ተወስኖ ከማገልገል የተሻለ ነው የእግዚአብሔር ጸጋ ግን ለሁሉም እንደየ አቅሙ እኩል ነው በማግባትና ባለማግባት ላይ የተመሠረተ አይደለም ከማግባት አለማግባት የተሻለ ጽድቅ እንደሚያስገኝ  የሚያስቡም ብዙዎች ናቸው ማግባትና አለማግባትን በመጽሐፍ ቅዱስ ስንመለከት ጋብቻ ግዴታ የሌለበት ትዕዛዝ ነው አለመግባት ግን ትዕዛዝ የሌለበት ፈቃድ ነው ወይም የፈቃድ ብቻ እንጂ ትዕዛዝ አይደለም እግዚአብሔር አዳምን ሦስት ትዕዛዛት አዘዘው

አንደኛው እርሱ የፈጠረለትን ሁሉ ብሉ ግዙ ብሎ ከሚስቱ ጋር አዘዘው ሁለተኛው መልካሙንና ክፉን የሚያሳውቀውን ዛፍ አትብላ ብትበላ ትሞታለህ ብሎ ለብቻው አዘዘው

ሦስተኛው ብዙ ተባዙ ብሎ ከሚስቱ ጋር የታዊ ትዕዛዝ አዘዘው ከነዚህም ከሦስቱ ትዕዛዛት አትብላ ያለው ግዴታና ቅጣት ያለበት ትዕዛዝ ሲሆን ቀሪዎቹ ሁለቱ ግን ግዴታና ቅጣት የሌለባቸው ትዕዛዛት ናቸው። በዚህም መሠረት ሰው በጋብቻ እንዲኖር ታዝዟል ሳያገባ ቢኖር እንደሚቀጣ የተሰጠ የግዴታ ቃል ስለሌለበት ግን ሳያገባ መኖር የራሱ ፈቃድ ነው እግዚአብሔርም ያለ ጋብቻ መኖርን ባያዝዝም ያለጋብቻ የመኖር ፈቃድን አልተቃወመም ::

ጌታችንም ሳያገቡ መኖር ስለሚችሉ ሰዎችም አስተምሮአል ከፈሪሳውያን በቀረበለት ጥያቄ መሠረት ባልና ሚስት መፋታት እንደሌለባቸው ሲያስተምር ሰምተው ደቀ መዛሙርቱ የባልና የሚስት ሥርዓት እንዲህ ከሆነስ ማግባት አይጠቅምም ብለው በጠየቁት ጊዜ ሳያገቡ መኖር ለሁሉም የተሰጠ አለመሆኑን ከነገራቸው በኋላ ሳያገቡ መኖር የሚችሉ ምን አይነት ሰዎች እንደሆኑ «በእናታቸው ማሕፀን ጃንደረባ ሆነው የተወለዱ አሉ፤ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ ስለመንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ›› ብሎ ከዘረዘረላቸው በኋላ ከነዚህ ዓይነት ሰዎች በስተቀር ያለ ጋብቻ መኖር ከባድ እንደሆነ በአጽንኦት ገልጧል ይህም ከእግዚአብሔር የተሰጠ ፅንጂ ሰው በራሱ ጊዜ ሊያደርገው ፅንደማይችል ሐዋርያት ላቀረቡለጥ ጥያቄ ምላሽ ሰጥቷል። ይህም በኦሪት ዘፍጥረት ላይ ከተመለከትነው ሃሳብ ጋር ተመሳሳይ ነው አስቀድመን እንዳየነው ብዙ ተባዙ ያለውን ትዕዛዙን ባይፈጽሙ የሚደርስባቸው አስገዳጅ ቅጣት እንዳለ በቃል ባይናገርም ሲፈጥራቸው በውስጣቸው አስገዳጅ ስሜት ጨምሮ ስለፈጠራቸው ይህነን ስሜት ታግሶ መኖር ከባድ እንደሆነ ሲናገር ነው‹‹ መታገስ የሚቻለው ይታገሰው›› ብሎ የተናገረው ማቴ19:10



# በሐዋርያው ጳውሎስ ትምህርት

ሐዋርያው ጳውሎስም ለቆሮንቶስ ሰዎች ‹‹ ስለዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱም ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት›› ብሎ ተጋብተው መኖር እንደሚገባቸው ካዘዘ በኋላ ስለባልና ሚስቱም ትምህርት ካስተማረ በኋላ እርሱ ግን እንደርሱ ሳያገቡ ቢኖሩ እንደሚወድ ነገር ግን ሳያገቡ መኖር ለተሰጣቸው ብቻ መሆኑን ‹‹ ሰው ሁሉ እንደኔ ቢሆን እወዳለሁ ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የጸጋ ስጦታ አለው ›› ብሎ ተናገሮ የተጋቡት ባልና ሚስት ደግሞ መፋታት እንደሌለባቸው የጌታ ትዕዛዝ መሆኑን ተናግሮ ስለጋብቻና ስለተጋቡት በሰፊው ካስተማረ በኋላ በድንግልና ስለ መኖርና አለመኖርም የራሱን ምክር ሰጥቷል እንዲህ ብሎ‹‹ ስለ ደናግልም የጌታ ትዕዛዝ የለኝም ነገር ግን የታመንሁ እንሆን ዘንድ ከጌታ ምረትን የተቀበልሁ እንደመሆኔ ምክር እመክራለሁ ::

እንግዲህ ስለ አሁኑ ችግር ይህ መልካም ይመስለኛል ሰው እንዲህ ሆኖ ቢኖር መልካም ነው በሚስት ታሥረህ እንደሆንህ መፋታትን አትሻ በሚስት አልታሠርህ እንደሆንህ ሚስትን አትሻ ብታገባ ግን ኃጢአት አትሠራም›› ብሎ ሐዋርያው ቃሉ የርሱም ምክር እንጂ የጌታ ትዕዛዝ አለመሆኑን ከገለጸ በኋላ‹‹ ስለ አሁኑ ችግር ይህ መልካም ይመስለኛል›› ብሎ‹‹ በሚስት ታስረህ እንደሆንህ መፋታትን አትሻ በሚስት አልታሰርህ እንደሆንህ ሚስትን አትሻ›› ብሎ ከማግባት አለመግባት እንደሚሻል መናገሩ በወቅቱ በክርስቲያኖች ላይ በነበረው ችግር ምክንያት በጋብቻ መኖር አስቸጋሪ ስለነበረ ነው ::

ችግሩን በስፋት ባይገልጸውም‹‹ ስለ አሁኑ ችግር›› ብሎ በትዳር ለመኖን ችግር እንደነበረና‹‹ ነገር ግን እንዲህ በሚያደርጉ በሥጋቸው ላይ መከራ ይሆንባቸዋል›› በማለት ጠቁሟል በመቀጠልም ካገቡት ይልቅ ያላገቡት ልቡናቸው ወደትዳር አጋሮቻቸው የተከፈለ ስለማይሆን ጌታን

ለማህበራዊ ኑሮ ነው እንጂ ያለህን ሸጠህ ተከተለኝ ያለውን የጌታን ቃል ፈፀመ ሊያስብለው አይችልም ሌላው ደግሞ የትዳር ጓደኛን ትቶ መሄድ ነው ጌታችን ያለህን ሁሉ ሸጠህ ለድሆች ሰጥተህ ተከተለኝ አለው እንጂ ሚስትህን ትተህ አላለውም ስለሚስት የተነሳ ነገርም የለም ጌታን መከተል ማለት ደግሞ የግድ ትዳርን መፍታት አይጠይቅም ለዚህም ማስረጃ የሚሆነን ያ ሰው ባለፀጋ ነበርና ንብረቱን ሸጦ ለድሆች ሰጥቶ ጌታን መከተል አቅቶት ሲመለስ አይቶ ጴጥሮስ ጌታችንን «እነሆ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ እንኪያስ ምን እናገኝ ይሆን» ብሎ ጠይቆታል ጴጥሮስ ሁሉን ትተን ተከተልንህ ማለቱ ታዲያ ሚስትን መፍታትን አያካትትም ምክንያቱም ጴጥሮስ ሚስስቱን ትቶ አይደለም የተከተለው እርሱ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ሐዋርያት ሚስቶቻቸውን ይዘው ነው የተከተሉት 1ኛቆሮ9:4

ስለዚህ ይህ ለምንኩስና የተጠቀሰው የጌታ ቃል ለምንኩስና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያ ሊሆን አይችልም ይላሉ መነኮሳቱ ደግሞ ምንም ጴጥሮስ ና ሌሎችም ሐዋርያት ሚስቶቻቸውን ትተው የተከተሉት ባይሆንም ከዚያው ጋር አያይዞ ጌታችን ጴጥሮስን ስለስሜም ብለው ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እህቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል የዘለዓለም ሕይወትን ይወርሳል ብሎ ስለተናገረ ሚስትንም ያለው ቃል ሚስትን ትቶ መከተል እንደሚገባ ያስረዳል ይላሉ::

ለዚህም ባለትዳሮች መልስ ሲሰጡ አንድ ሰው በጌታችን አምኖ ጌታን ለመከተል ሲያስብ ሌሎች ቤተሰቦቹም ሆኑ ሚስቱ የሚቃወሙት ከሆነና ከእርሻው የሚያገኘውም ጥቅም እንቅፋት የሚሆንበት ከሆነ ጌታ ስም ሌሎች ቤተሰቦቹንም ሚስቱንም የእርሻውንም ጥቅም ትቶ መከተል ዋጋ እንዳለው ሲያስረዳ ነው እንጂ ሚስትን መፍታት ሲያስተምር አይደለም ሚስትን መፍታት ኃጢአት እንደሆነ ደግሞ እራሱ ጌታችን «ሰው እናትና እባቱን ይተዋል ከሚስስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ» የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን ስለዚህ አንድ ስጋ ናቸው እንግዲህ ወደፊት



ሁለት አይደሉም እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየውም ብሎ ተናግሮአል በማለት ይከራከራሉ::ማቴ19:5 ዘፍ2:24

በሌላም በኩል ጌታችን ተከታዮቹ በፈቃዳቸው ሁሉን ትተው ቢከተሉትም ምድረ በዳ (ገዳም) ይሂቸው አልገባም እዚያው በዓለም እያሉ ከአለም ለያቸው እንጂ «እኔም ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉምና ዓለም ጠላቸው ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልልም» ብሎ ዮሐ17:14 ስለዚህ እዚሁ በዓለም እያሉ በክርስቶስ አምኖ ከዓለም መለየትን እንጂ ትዳርን ፈትቶ ንብረትን ተካፍሎ ገዳም ገብቶ መቀመጥን ክርስቶስ አላስተማረም ይላሉ::

ምንኩስና የክርስትና ትምህርት ሳይሆን ከቡድሂዝም ሃይማኖት ትምህርት የተወሰደ ነው የሚሉም አሉ ከዚህ በላይ የሁለቱን ወገን ክርክር ማቅረቤ አንባቢ የራሱን አስተያየት እንዲሰጥ ለመጋበዝ ነው:: ከላይ የተነሱትን ክርክሮች አንብቦ ከታሪኩ ጋር እንዲያነጻጽር ታሪኩ እንደሚከተለው ቀርቧል::

## <u>የምንኩስና ታሪክ</u>

ምንኩስና በግብጽ በረኃ በሲና በፍልስጥኤም የተጀመረ የመጀመሪያዎቹ የመነኮሳት ሰፈራዎች/ ገዳማት/ የተመሠረቱት በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ አባ እንጦንስ በተባለ መነኩሴ አማካኝነት ግብጽ ውስጥ ነው ከዚህ ግብፅ ውስጥ ታቢኒዚ በተባለ ቦታ በ323 ዓ.ም አባ ባኩሚዝ (ጳኩሚስ) ሌላ ገዳም መሠረተ የመጀመሪያዎቹ መነኮሳት ተራ ምዕመናን ነበሩ ለገዳሙ የቅዳሴ አገልግሎት የሚያገለግሉ ከመካከላቸው አንዳንዶቹ ለቅስና ይሾማሉ ይህ በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የነበረ ልማድ ሲሆን በምዕራብ በኩል ግን መነኩሴ የሚሆኑት አብዛኛውን ጊዜ ካህናት ነበሩ ለምሳሌ ኢየሱሳውያን የተባሉት መነኮሳት ቀሳውስት ናቸው::

በምሥራቅና በምዕራብ መነኩሳት መካከል ያለው ዋናው ልዩነት ደግሞ የኦርቶዶክስ መነኮሳት በጾም በጸሎት በስግደትና በንስሓ የሚኖሩ ሲሆን

የምዕራብ መነኮሳት ከመንፈሳዊ/ ስማያዊው/ ዝንባሌ ሌላ በዚህም ዓለም ተግባር ለምሳሌ በሥነ ጥበብ በተግባሬ እድ ድሆችን ሲረዱ በሚያስችሉ ድርጅቶች ላይ የበለጠ ትኩረት ይሰጡ ነበር፡፡

የመጀመሪያው ገዳም መሥራች የአባ እንጦንስ የሕይወት ታሪክ በታላቁ የእስክንድርያ ፓትርያርክ በቅዱስ አትናቴዎስ ተጽፏል በታሪኩ መሠረት አባ እንጦንስ በርካታ ልጆች ካሏቸው ወላጆቹ ነው የተወለደው፡፡ አንድ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄድ በማቴዎስ 19 ፡21 ላይ «ኢየሱስም ፍጹም ልትሆን ብትወድ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ መጥተህም ተከተለኝ አለው» ተብሎ የተፃፈው ሲነበብ ደረሰ ይህም የወንጌል ቃል ራሱን እንደጠራው ስለአመነ በፍጥነት ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤቱ ተመልሶ የ 300 ጥማድ ያህል ከወላጆቹ የወረሰውን ርስት ለድሆች ለጎረቤቶቹ አካፍሎ መቃብረ ሙታን ወደ ነበረ አንድ ዋሻ ውስጥ ዘጋ ይህንም ያደረገበት ምክንያት ከዚሁ ቦታ አጋንንት በብዛት ያሉበት መሆኑን ስለአመነ በክርስቶስ ኃይልም ድል እንደሚያደርጋቸው ስለተገነዘበ ነው፡፡

ቀጥሎ ' ባሉት ዓመታት ለኢትዮጵያ ይሾሙ የነበሩ ጳጳሳት የሚመረጡት ከቀይ ባህር 40 ኪ.ሎ ሜትር ያህል ርቆ ይገኝ ከነበረው ከዚሁ ከአባ እንጦንስ ገዳም ነበር፡፡ በዚሁ በአባ እንጦንስ ዘመን ለውትድርና ተገዶ የነበረው አባ ጳኩሚስ የውትድርናን መራራነት ከተመለከተና በአባ እንጦንስ ገዳም ያለውን የምንኩስናን ጣዕም ከተረዳ በኋላ በዚያው በሲና በረኃ የራሱን ገዳም መሥርቷል፡፡

በዚህም በማኅበረ መነኮሳቱ ውስጥ የተግባረ እድ ሙያ ይከናወን ነበር፡፡ የገዳሙ አበ ምኔት/ አስተዳዳሪ/ ለሥራው የሚያስፈልጉትን መሣሪያዎች የማቅረብና የተመረቱት ነገሮችም ተሸጠው ለገዳሙ አገልግሎት እንዲውሉ ያደርግ ነበር፡፡



ኃጢአት የመነኮሳቱን ኑሮ እንዳያናጋው እያንዳንዱ መነኩሴ በየቀኑ የሠራውን ኃጢአት እንዲናገር ተደንግጎ ነበር ቤተ-ክርስቲያንም ይህን ኃጢአትን ፣ የመናዘዝ ልማድ የወሰደችው ከዚሁ ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል፡፡

ይህም የምንኩስና ሥርዓት በፍጥነት እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ ተስፋፋ ይኸውም በፍልስጥኤም ውስጥ በጋዛ ነበር ሂላርዮስ የተባለው ሰው ገና የአሥራ አምስት ዓመት ወጣት ሆኖ እያለ በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን የተፈጸመውን የክርስቲያኖችን መከራና ስደት አይቶ ከአረማዊነት ወደ ክርስትና ተመልሶ እርሱም ግብጽ አገር ወደሚገኘው ወደ አባ እንጦንስ ገዳም ሄዶ የምንኩስናን ሥርዓት ካጠና በኋላ በ330 ዓ.ም ከጥቂት የግብጽ መነኮሳት ጋር ወደ ፍልስጥኤም ሀገር ተመልሶ በጋዛ ገዳሙን መሥርቷል የሂላርዮስ ታሪክ (ሂሪኒምስ) በተባለው የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ቤተክርስቲያን አባት በ390 ዓ.ም ተመዝግቧል፡፡

በኢየሩሳሌም በሙት ባህር መካከል የሚገኘው የይሁዳ በርኃ በ4ኛውና በ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በብዙ ገዳማት የተከበበ ስፈረ መነኩሳት ሆኖ እንደነበር በታሪክ ታውቋል በዚሁ ጊዜ በ330 ዓ.ም ተማሪ የነበረ ሀሪቶን የተባለ ሰው ኢየሩሳሌምን ለመሳለም በይሁዳ በረሃ ሲያልፍ ወንበዴዎች ደብድበው ከማረኩት በኋላ ወደ አንዱ ዋሻ ይዘውት ገቡ ከዋሻውም ውስጥ ወይን አግኝተው ከጠጡ በኋላ ወይኑ የተመረዘ ኑሮአል ሁሉም ሞቱ ሀሪቶንም ይህን ከተመለከተ በኋላ ቀሪውን ሕይወቱን በምንኩስና ለማሳለፍ ቆረጠ በዚሁ ገዳም ዘግቶ ተቀመጠ ሀሪቶን የተወለደው ታናሽ እስያ ውስጥ ነው፡፡

ታላቁ ባስልዮስ ትምህርቱን አቴንስ ውስጥ ካጠናቀቀ በኋላ በ356 ዓ.ም ከወላጆቹ የወረሰውን ርስትና ጉልት እንዲሁም ቤት ለመነኮሳት መኖሪያ አድርጎ በግብጽ በኢየሩሳሌም በሶርያ እተዘዋወረ ሥርዓት ገዳማትን በብዙ አጥንቷል ከዚያም ከተመለሰ በኋላ 55 አንቀጾች ያሉት ሥርዓተ ገዳም ጽፎ ለገዳሙ መተዳደሪያ እንዲሆን አድርጓል ይህም የባስልዮስ ሕግ በመባል

እስካሁን ይታወቃል በፍትሐ ነገሥት የሚገኘው የመነኮሳት ሥርዓትም ይህን መሠረት ያደረገ ነው። /ፍ.ነ አንቀጽ 10/

ኦኮኢሚትን እየተባለ የሚጠራውና በሜስፓታሚያ/ በሁለቱ ወንዞች ጤግሮስና ኤፍራጥስ መካከል የሚገኘው ሀገር/ አካባቢ የተነሣው እንቅስቃሴ ደግሞ መነኮሳት ጭራሽ ከእንቅልፍ እንዲወገዱ የሚቀሰቅስ ነበር ይኸውም ጌታ ሳታቋርጡ ተግታችሁ ጸልዩ ያለውን መነሻ በማድረግ ነው። /ሉቃ 18፡1/

በ463 ዓ.ም የቁስጥንጥንያ ቆንሲል የነበረው ስቱዲዮስ የተባለው ቁስጥንጥንያ ውስጥ ገዳም ለመመሥረት ፈልጎ እነዚህን አኮኢሚትን የተባሉትን መነኮሳት አስመጣ በርሱ አማካኝነት የተመሠረተውና በስሙ ስቱዲዮስ ገዳም እየተባለ የሚጣረው ገዳም በዚሁ አካባቢ ለሚገኙ ገዳማት ሁሉ ምሳሌ እንዲሆን በ799 ዓ.ም ተወስነ ይህም የሆነው ታላቁ ቴዎጾር የገዳሙን አበምኔትነት ከተረከበ ጊዜ ጀምሮ ነው።

በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ የዚሁ ገዳም ሥርዓት ወደ ኢትዮጵያና እንዲሁም ወደምዕራብ ሀገሮች ተሰራጭቷል የሩስያው ቤኒዲግት ሱቢያኮ ከተባለው ቦታ በገበሬዎች አማካኝነት እንዲሰደድ ሲደረግ ምንቴ ካሲኖስ በተባለው ቦታ ቤትና የቦታ ስጦታ ስለተደረገለት በ529 ዓ.ም መነኮሳትን በማሰባሰብ ገዳም መስርቷል ሞንቲባሲያስ በሚባለው የምዕራብ አውሮፓ የሚገኙ ቤኒዲግቱስ ገዳማት ሁሉ መስራችና የበላይም መሪ አስተዳዳሪ ነው ቤኒደግቱስ ያዘጋጀው ሥርዓተ መነኮሳት አብዛኛውን ጊዜ የተወሰደው ታላቁ ባስልዮስ ከጻፈው ሥርዓተ መነኮሳት ነው በዚህ ጊዜ በኢትዮጵያ የምንኩስና ሥርዓት ማበብ ጀምሮ ነበር ይህም የሆነው አቡነ አረጋዊ የተሣቱ / ዘጠኙ/ ቅዱሳን መሪ በመሆን ወደ አክሱም ከመጣ በኂላ ነው የመጣውም በቢዛንስ መንግሥት ይሰደዱ ከነበሩት የሶርያ ክፍል ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል። የኢትዮጵያ ሥርዓተ ገዳም የሚያዘነብለው ሶርያ ወደሚገኙ ገዳማት ሲሆን መጽሐፈ መነኮሳትም የተጻፈው ታላላቆቹ ሶርያ ገዳም አባቶች ያዕቆብ



ዘሥሩግና ፊሎክስያስ ዘማአቡክ ከጻፉት ሥርዓተ መነኮሳት እየተተረጎመ ነው።

ምንኩስናን ወደ ምዕራብ የወሰደው ከ296-372 የነበረው ሊቀ አትናቴዎስ ወደሮም በተሰደደበት ጊዜ ነው ይኸውም አስቀድሞ ወደ በረኃ ሄዶ ሥርዓተ ምንኩስናን ከአባ እንጦንስ ተምሮ ስለነበር ነው።

# ምዕራፍ ሶስት

## ምንኩስና በስርዓት መጻሕፍት

## የምንኩስና አፈጻጸም ሥርዓት

አሲረ ምንኩስና ቅዱስ የሚባል የምንኩስና ሥርዓት መጽሐፍ አለ በዚያ መሠረት የምንኩስና ሥርዓት ሲፈጸም ምንኩስና የሚቀበለው ሰው መጀመሪያ በፈቃዱ ከዓለም መለየቱን ከዚያም የምንኩስና ኑሮው ምን ዓይነት እንደሚሆን በቃል ያስረዱታል በጽሑፍም ያነቡለታል ይህንም ድምጹን ከፍ አድርጎ መስማማቱን ሲገልጽ ከፊታቸው ያጋድሙትና ጸጉሩን ይላጩታል ቀጥሎም ለምንኩስና በሚሆነው ልብሱና በሰውየው ላይ እንደሞተ ሰው ጸሎተ ፍትሐት ይጸልዩለታል ከዚያም በመጀመሪያ የገዳሙ አበምኔት (መምህር) በመቀጠል በፍትሐቱ የተገኙት ሁሉ ይባርኩትና ልብሱን ያለብሱታል ከዚያ በኋላ የመጨረሻው ጸሎት ተጸልዮለት የምንኩስና ሕይወት ኑሮውን ይጀምራል እንደቀድሞው ሕግ ከሆነ ከጥቂት ዓመታት በኋላ አስኬማ የሚባል ልዩ ልብስ ይሰጠውና ወደ ከፍተኛው ደረጃ ይሸጋገራል አስኬማ ከነት /የተለፋ ቆዳ/ የሚሰራ 12 የመስቀል ምልክት ያለበት ነው አሁን አሁን ግን ማንኛውንም የምንኩስና ልብስ አስኬማ ይሉታል።

## የአኗኗር ስርዓት በፍትሐ ነገሥት

ከላይ ባየነው የምንኩስና ታሪክ እንደተመለከተው ምንኩስና በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጀመረ የመናንያን የአኗኗር ስርዓት በመሆኑ በመጽሐፍ

ቅዱስ የተሰጠ ስያሜና ስርዓት ባይኖረውም በጊዜው የነበሩ አበው መነኮሳት እንዴት መኖር እንዳለባቸው ሥርዓት ሠርተዋል እንደዛሬው የምንኩስና ሥርዓት መረን አለቀቁትም የዛሬው ምንኩስና መረን መለቀቁን የምናየውም የቀድሞዎቹ አበው በሰሩት በራሱ በምንኩስና ስርዓት ነው እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ አይደለም ምክንያቱም ስለ ምንኩስና በመጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠ ስያሜም ሆነ ስርዓት ስለሌለ ነው አበው እንደ መነሻ ከጠቀሷቸው አንድ አንድ ቃላት በስተቀር ይህን የቀድሞውን ምንኩስና የአኗኗር ሥርዓት በሚከተሉት ነጥቦች ከፋፍለን እንየው:-

## ቦታና የቦታው ሥርዓት

የመነኮሳት መኖሪያ ቦታ ገዳም ይባላል ገዳም ማለት የግዕዝ ስሙ ሲሆን ትርጉሙ ምድረበዳ ነው ሰው የማይኖርበት ማለት ነው ግዕዙ መጽሐፍ ቅዱስ ገዳም የሚለውን አማርኛው ምድረ በዳ ይለዋል ማቴ 3:1፤4፤1 ምድረ በዳ ማለትም ሰዎች የማይደርሱበት ማለት ነው ባስልዮስ በጻፈውና የእርሱን ጽሁፍ መሠረት አድርጎ በፍትሐ ነገሥት በተጻፈው የመነኮሳት የአኗኗር ስርዓት መሠረት መነኮሳት ከገዳም እንዳይወጡ የገዳሙ ዘበኛ እንዲጠብቅና ከውጭም ያለገዳሙ አስተዳዳሪ ፈቃድ መግባት እንደሌለባቸው ወጥተው ወደ ገጠር ወይም ወደ ከተማ ከገቡ ግን ምንኩስናቸውን ትተው ሕዝቡን መስለው መኖር እንዳለባቸው ይናገራል:: /ፍ. ነገ አንቀጽ 10/

## አመክሮ

አመክሮ ማለት የግዕዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ፈተና ማለት ነው ይኸውም አንድ ምዕመን ለምንኩስና ወደገዳሙ ሲገባ ከመመንኮሱ በፊት ለምንኩስና ብቁ መሆኑን አለመሆኑን ሥርዓተ ምንኩስናውን በመለማመድ ራሱን የሚፈትንበት የምንኩስና ቅድመ ዝግጅት ነው ይህ ቅድመ ዝግጅት ወደ ገዳም ሲገባ ጀምሮ ከሚደረግለት አቀባበል ይጀምራል ስለ አቀባበሉ በፍትሐ ነገሥት እንደሚከተለው ሰፍሯል::‹‹ ምንኩስና በግድ ያይደለች



የፈቃድ ናት አንዱ እንኳን መንኩሶ በውስጡ ይኖር ዘንድ ወደ ገዳም በደረሰ ጊዜ ከየት እንደመጣ ሥራውም ምን እንደሆነ ወደ ገዳማቸው በምን ምክንያት እንደተጠጋ ልጅ ሚስት እንዳሉት ስለዘመኑም ችግር ከልጆቹና ከሚስቱ ሊያመልጥ ፈልጎ እንደሆነ የገዳሙ መምህር በጽኑ ይመርምረው.... ሚስት ያለችው ቢሆን መመንኮሱንም የማትወድ ብትሆን አይቀበሉት ከሚስቱ የተነሣ ህመምና ክፉ ነገር ቢሆንበት ግን ሊድን ወዶ ከእርሷ ቢለይ ይቀበሉት.... ምንኩስናን የወደደ ሁሉ ልጆች የሌሉት ከሆነ ከመመንኮስ በፊት እንደወደደ በገንዘቡ ይዘዝ ከመነኮሰ በኋላ ግን ገንዘቡ ሁሉ ለገዳሙ ይሆናል::

በምርመራውም አግብቶ የነበረ ከሆነና ሚስቱን የተወበትም ምክንያት አሳማኝ ከሆነ ወይም ሙታበት ከሆነ ያላገባ ከሆነ ደግሞ በድንግልና ፀንቼ እኖራለሁ ካለ በገዳሙ እንዲኖር ይፈቀድለታል የሥጋ ዘመዶቹንና የዚህ ዓለምን ነገርም ሁሉ መርሳት እንዳለበት ይመከራል አመክሮውን ይጀምራል ከመመንኮሱ በፊት እንደ ገዳሙ ሥርዓትና እንደርሱ ሁኔታ ከሦስት እስከ ሰባት ዓመት ገዳሙን እያገለገለ በአመክሮ ይቆይና ይመነኩሳል ከዚህ በኋላ ከገዳሙ መውጣት አይፈቀድለትም

## አመጋገብ

ስለመነኮሳት አመጋገብ ፍትሐ ነገሥት እንዲህ ይላል

ለገዳሙ እርሻ የሚያርሱ መነኮሳት የሆኑ እንደሆነ በቀን ሁለት ጊዜ በስድስት ሰዓትና በአሥራ ሁለት ሰዓት ይመገቡ የማያርሱ የሆኑ እንደሆነ በቀን አንድ ጊዜ ብቻ በዘጠኝ ሰዓት ወይም በአሥራ ሁለት ሰዓት ይመገቡ ሥጋ ለዘለዓለም አይብሉ ወይን ሐዋርው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንዳዘዘው ለመድኃኒት ያህል ይቅመሱ ይላል 1ጢሞ 5:23 ፍ. ነገ አንቀጽ 10

## አለባበስ

የመነኮሳት ልብስ እንደ ዮሐንስ መጥምቁ ማቅ ይልበሱ ወገባቸውን ከቆዳ በተሠራ መታጠቂያ ይታጠቁ ይላል ዮሐንስ ከግመል ፀጉር የተሠራ

ማቅ ይለብስ ወገቡንም በጠፍር ይታጠቅ ነበርና /ማቴ 3፤4/ አያጊጡ ሽቱ አይቀቡ ይላል /አንቀጽ 10/

## ጸሎትና ሥራ

ለጸሎት ለመስገድ የተዘጋጁ ይሁኑ ወታደር ለጠብ ማታና ቀን ለውጊያ ሰዓት እንደሚዘጋጅ በማለዳ ወደሥራ ይገስግሱ በቀትር ጊዜ ይረፉ ከጸለዩ በኋላ ይመገቡ ፀሐዩ እስከሚቀዘቅዝም ይረፉ ፀሐዩ ከቀዘቀዘ በኋላ እስከ ምሽቱ ድረስ ይሥሩ ከዚያ በኋላ ፀልየው ይመገቡ ይላል /አንቀጽ 10/

## ሹመት አለመፈለግ

መናኝ የክህነት የአበ ምኔትነት ሹመት መውደድ አይገባውም የሹመት ፍቅር ሰይጣናዊት በሽታ ናትና በዚህ በሽታ የተያዘ ሰው ካህናትና ሹማምንት ሊሆኑ በሚገባቸው ላይ ቀናተኛ ይሆናል ሰው መክሮ ያነሳሰባቸዋል በነርሱ ሹመት ይተካ ዘንድ ሞታቸውን ይወዳል ሹመቱ ባልሆነለት ጊዜ በርሱና በነርሱ መካከል ችግር ይፈጥራል ከዚህ መጥፎ ተግባር ይራቅ ለሹመት በሚበቃ እድል እግዚአብሔር ከወደደ እርሱ ብቻ የሚሾመውን ያውቃል ይላል /አንቀጽ 10/

## ከተቃራኒ ፆታ መለየት

አስቀድመን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንፃርም እንዳየነው መነኩሴን መነኩሴ ከሚያሰኙት ዋና ዋና ነገሮች አንዱ ከተቃራኒ ፆታ መለየት ነው በሥርዓተ መጻሕፍትም አመክሮ በተሰኘው ክፍል እንዳየነው ወደ ምንኩስና ሲገባ ሚስት ያለችው ከሆነ ሚስቱ ፈቅዳለት ወይም አሳማኝ በሆነ ምክንያት ከርሷ ጋር መኖር የማይችል ከሆነ ፈቶ ነው ወደ ገዳም መግባት ያለበት ከዚያም በኋላ ወንዶች ከሴቶች ሴቶች ከወንዶች ጋር ከማይተያዩበት ቦታ ነው መኖር ያለባቸው፡፡

ፍትሐ ነገሥት ‹‹ከሴቶች ጋር አይጎራብቱ ከመነኮሳት ወገን ከሴቶች ጋር እየኖረ ይህ ነገር ድል አይነሣንም አይበል ይለያዩ ካልተለዩ ግን ሁለቱም /ይወገዙ/ ይላል ሴቶችንም ሳቅ አያብዙ ወንድ ካለበት ቦታ አይቀመጡ



ይላቸዋል /አንቀጽ 10/ እስከዚህ ያየነው በፍትሐ ነገሥት የተሠራውን ሥርዓተ ምንኩስና ነው፡፡

## በሃይማኖተ አበው

ሃይማኖተ አበው ደግሞ ስለመነኮሳት በተጻፈው ክፍል የሚከተለውን ይናገራል፡፡ መነኮሳት ሆነው ቢነግዱ ግን በመከራ የሚገኘውን ክብር ለማግኘት የተቀበሉትን የተቀደሰ ማዕረጋቸውን አዋረዱ አንተ መነኩሴ ወይም አንተ ካህን ደዌ /ሕማም/ የሌለብህ ከሆንህ እንቅልፍህ ሁል ጊዜ በመጠን ይሁን ከሁሉ አስቀድሞ ወደተግባረ ነፍስና ወደ ተግባረ እድ ተመለስ እርሻን ቁፋሮን ያዝ ሰነፍ አትሁን በእጅህ ከሰራኸው ሥራ ከራስህ አትርፈህ ለድሆች ለደካሞች ለመጻተኞች የምትሰጠውን ለአንተም የምትሻውን ታገኝ ዘንድ፡፡

አንተ መነኩሴ ከአኃው ጋር በአንዲት ገዳም በአንድነት ሳለህ ከርስትህ ከሰበሰብከው በእጅህ ከአገኘኸው ይህን የመሰለ ቢኖርህ በጌታ ትዕዛዝ አንተ አብርሃቸው ካለህ ከአንደኛው ከርሱ ምንም አትሰውር ያለህን ሁሉ ሽጠህ ዋጋውን ለማኅበሩ/ አበርክት ከአኃው ጋር በአንድነት ብትኖር ለአንተ ብቻ የሆነ እርሻ ወርቅ ብር ቢኖርህ ወንድሞችህ ያላገኙት ከዚህ ዓለም ገንዘብ ማንኛውም ቢኖርህ አንተ መናኒ አይደለህም ይህን ዓለም ፈቃዱንም በእውነት አልናቅህም አንተ ዘበትህ አጋንንትም ዘበቱብህ እንጂ፡፡

ከዚህ በላይ ያየናቸው በፍትሐ ነገሥትም ሆነ በሃይማኖተ አበው የተመዘገቡት ምንጫቸው የባስልዮስ የሥርዓተ ምንኩስና መጽሐፍ ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት

# ምናኩስና ዛሬ በኢትዮጵያ

ባለፈው ምዕራፍ ምንኩስና ታሪካዊ አመጣጡን እንዲሁም የአኗኗር ሥርዓቱን ያብራራሁት ዛሬ በሀገራችን የሌቦችና ወንበዴዎች መጠለያ ከሆነው የምንኩስና ሥርዓት ጋር እያነፃፀሩ ምዕመናን እውነታውን ተረድተው አንደኛ በጌታችን ደም ላይ የተመሠረተችው ወንጌላዊትና ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን በምንኩስና ስም ጌታችን እንዳለው‹‹የሌቦችና የነፍሰ ገዳዮች ዋሻ›› መሆኗን ማቴ 21፡12-16፣የሐ 8÷44

ሁለተኛ ዛሬ የሌቦችና የወንበዴዎች ጭንብል ሆኖ ሥርዓቱ ቢበላሽም የምንኩስናን ሥርዓት ቀደም ብለን እንዳየነው ምንም የፈቃድ የኑሮ ሥርዓት ቢሆንም ሰዎች ከኃጢአት ርቀው የሚኖሩበት ሥርዓት መሆኑን ተረድተው ራሳቸውን ከሌቦችና ከወንበዴዎች እንዲጠብቁ ለማስገንዘብ ነው ሌቦች ነፍሰ ገዳዮች ወንበዴዎች ብየ ደፍሬ ስናገር ብዙ ሰዎችን ያስቀይም ይሆናል እኔ ግን አይደለሁም ጌታ እንጂ ሥራቸው ጌታ እንደተናገራቸው ወንበዴዎች ካልሆኑ ተሳስቻለሁ ሥራቸው እንደነዚያ ከሆነ ግን ጌታ የተናገረውን መናገር ምን ያሳፍራል ሐዋርያው ጳውሎስ በወንጌል አላፍርም ብሎአልና አሁንም ለወንጌል ከተጠራን በወንጌል ማፈር የለብንም ቤተ ክርስቲያን የወንበዴዎች ዋሻ ስትሆን ዝም ብለን ስናይ የራሳችን ድርሻ መወጣት ይኖርብናል እስዚያ ግን የወንበዴዎች ተባባሪ መሆናችን ነው የውንብድና የነፍስ ገዳይነት ሥራቸውን ወደፊት እናየዋለን በቅድሚያ ያሁኑ ሥርዓት ከቀድሞው ሥርዓት ጋር ያለውን ልዩነት እንይ

## የመነኮሳት ዓይነቶች

ቀድሞ ምንኩስናውም ሆነ በመነኮሳቱ የአኗኗር ስርዓት አንድ አይነት ነበር ዛሬ በሀገራችን የሚታዩትን መነኮሳት ግን ስራቸውንና አኗኗራቸውን መሰረት በማድረግ በአራት ክፍሎ ማየት ይቻላል እነርሱም፡-

አባ ዓለም ለምኔ



አባ ዓለም በቃኝ

አባ ዓለም በዘዴ

አባ ቆብ አልባ ናቸው

**አባ ዓለም ለምኔ፡-** በድሮው የምንኩስና ሥርዓት መሠረት ሚስት ሳያገቡ ቤት ሳይሠሩ በብሕትውና ተወስነው በገዳም የሚኖሩት ናቸው።

**አባ ዓለም በቃኝ፡-** በዚህ ዓለም ሚስት አግብተው ቤት ሠርተው ኑረው በኋላ ሚስት ስትሞትባቸው ወይም ስትከዳቸው ወይም በበሽታም ምክንያት ይህን ዓለም በቃኝ ብለው መንነው ገዳም የሚገቡና ወይም በአሉበት አካባቢ መንኩሰው ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ ናቸው እነዚህ ዓለምን አይተው በቃኝ ብለው የተዋት ስለሆኑ በዓለም ሁነው ቤተክርስቲያንን ቢያገለግሉም ብዙም ሲያጭበረብሩና ምዕመናንን ሲያታልሉ ዓይታዩም ቤተ ክርስቲያን በማስተዳደር በኩልም አስቀድመው ቤተሰብን በማስተዳደር ችግሩን ስለሚያውቁት (የምዕመናን) ሃሳብ የመረዳትና የማዘን ዝንባሌአቸው የተሻለ ነው ቤቱን ማስተዳደር ያልቻለ የእግዚአብሔርን ቤት ማስተዳደር እንዴት ይችላል እንዳለው ሐዋርው ጳውሎስ ቤተሰብ ያስተዳድሩ የነበሩ መሆናው የተሻሉ ሲያደርጋቸው ችሏል 1ጢሞ 3÷4 ከጥቂቶቹ በቃን ካላሉት በስተቀር

**አባ ቆብ አልባ፡-** እነዚህ የምንኩስና ልብስ ሳይለብሱ ቆብ ሳይደፉ በድንግልና ተወስነው ትምህርት በማስተማር ቤተክርስቲያንን የሚያገለግሉ መምህራን ናቸው እነዚህ ለሀገራችንም ሆነ ለቤተክርስቲያናችን ባለውለታዎች ናቸው ዘመናዊ ትምህርት ወደ ሀገራችን ከመግባቱ በፊት ቤተ ክርስቲያናችን ብሎም ሀገራችን በፊደል በሥነ-ጽሑፍ በቋንቋ ራሷን ጠብቃ እንድትቆይ አድርገዋል የቀድሞዎች። የዛሬዎቹ መሰሎቻቸውም በማስተማር ተጠምደው የራሳቸውን አስተዋጽኦ እያበረከቱ ነው የቤተክርስቲያኗ ገንዘብ በእነ አባ ዓለም በዘዴ ቁጥጥር ሥር ስለሆነና እንደድሮው ለምኖ ለመብላትም ሕዝቡ ስለ ደኸየ‹‹ የአባትህ ቤት ሲዘረፍ

አብረህ ዝረፍ እንዲሉ›› እነርሱም እንደነ አባ ዓለም ለምኔ ለመሆን ተማሪዎቻቸውን እየበተኑ ወደ ከተማ በመፍለስ ላይ ናቸው እንጂ እነ አባ ዓለም በዘዴ እስከ ሦስት ሺህ ብር ይከፈላቸዋል እነርሱ ግን የመቶ ብር ደመወዝ የሚሰጣቸው አጥተው የቤተክርስቲያኗን ትምህርት ማስተማር ትተው በመኮብለል ላይ ናቸው ::

አንዳንዶቹ ደግሞ ወደርሻና ንግድ በመሰማራት ላይ ናቸው እነ አባ ዓለም በዘዴ ፊደልን እንኳን አስተካክለው ሳይቆጥሩ ነው ባቋራጭ ቆባቸውን በመጫን ወፍራም ደመወዝ የሚከፈላቸው ወይም የምዕመናንን ገንዘብ ያለከልካይ የሚካፈሉ እነርሱ ግን አሥርና ሃያ ዓመት ተምረው መቶ ብር እንኳን የሚሰጣቸው አጥተው ነው የሚራቡት ታዲያ እነዚህ መምህራን ምን ያድርጉ የችግሩን አሳሳቢነት የቤተክርስቲያንን ልጆች ሊያሳስብ ይገባል እያልሁ ወደ ተነሣሁበት ነጥብ ልመለስ

አባ ዓለም በዘዴ፡- እነዚህ ጌታ ፍሬ እንዳጣባት የለመለመች በለስ በአለባበሳቸው ጀርፈፍ ብለው የጽድቅ ፍሬ የማይገኝባቸው ናቸው እስኪ ይህን ሃሳብ በጥንቱ ትርጓሜ ስልት ልግለጸው ለሊቃውንቱ በቀድሞው በለስ እስራኤል ናት ተብሎ ተተርጉሟል አሁን በሀገራችን ደግሞ መነኩሴ ተብሎ ቢተረጎም የሚስማማ ይመስለኛል::

የቃሉ የመጨረሻ አንድምታ ሆኖ እንዲህ ቢቀጥልስ አንድም በአንጻረ በለስ ረገሞ ለመነኮስ ያሰኛል በለስ መነኩሴ ቅጠል ጀርፋፋው አለባበሳቸው ጌታ ሄዶ ፍሬ እንዳጣባት የዛሬ መነኮሳትም የጽድቅ ፍሬ አይገኝባቸውምና ፍሬ አይገኝብሽ እንዳላት‹‹ ግብሩ ፍሬ ዘይደሉ ለንስሐ›› እንዲል ንስሐ ገብተው የጽድቅ ፍሬ አያፈሩምና ማቴ 3፡8::

አንድም ፍሬ ልጅ ነው ብሎ መነኮሳት ልጅ አይወልዱምና ፍሬ አይገኝብሽ አላት እነ አባ ዓለም ለምኔ እንጂ እነ አባ ዓለም በዘዴማ እስመ ብዙኃት አንስቲአ ሆሙ ወአልቦ ትልቁ ለደቂቆሙ ሚስቶቻቸው ብዙ



ልጆቻቸው ቁጥር የላቸው እንዲሉ ይፈለፍሉ የለምን ቢሉ እናቱ ካላጋለጠች ልጁ አባቱን ካልመሰለ አይታወቅምና ካልታወቀ ብሎ ደግሞም ቢወልዱም አያሳድጉምና ልጅ የላቸውም አለ አንድም ምዕመናንን በመልካም ሥነ-ምግባር በመንፈሳዊ አኗኗር አይወልዱምና ፍሬ አይገኝብሽ ብሎ ተናግሮባቸዋል::

## ለጥቋቁር ርግቦች የተነገረ ትንቢት

እነዚህ ዛሬ በምንኩስና ስም በከተማ ለተሰማሩ ሰዎች ከብዙ ዘመናት በፊት እንደዚህ ሆነው እንደሚመጡ ትንቢት መሰል ንግርት ተነግሮላቸዋል ያውም ከነአለባበሳቸው ትንቢቱን አባ ጳውሊ የተባለ ባህታዊ ራዕይ አይቶ ለአባ እንጦንስ እንደነገረው ነው ፊልክስዮስ በተባለው መጽሐፍ መቅድም ላይ ሰፍሮ የሚገኘው ምንም እንኳ ትንቢት የተባለው ነገር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የተነገረ ነው ለማለትባንደፍርም ሰዎቹ ራሳቸው በራሳቸው ባሕርይ ላይ ይሆናል ብለው የተናገሩት ግን እውን ሆኖ ታይቷል ::

ንግርቱ ( ትንቢቱ ) እንዲህ ነው::

አባ እንጦንስ አባ ጳውሊ ወደ ተባለው ባህታዊ ይሄዳል አባ ጳውሊ ሊገናኘው ከበኣቱ ሲወጣ ከዚያ በፊት ተደርጎ የማያውቅ የምንኩስና ልብስና ቆብ አድርጎ ያየዋል እርሱም መላክ አሳይቶት ሰርቶ እንደለበሰ ካስረዳው በኋላ እስኪ ይህ ነገር ከኔ ብቻ የሚቀር ነው ወይስ ወደሌላ ይተላለፍ እንደሆነ ወደ እግዚአብሔር አመልክትልኝ አለው ይላል :: እሺ ብሎ አመለከተለት ወዲያውም ተገልጾለት ፈገግ አለ ምን አየህ አለው ነጫጭ ርግቦች በጠፈር ሞልተው አንተ እየመራሀቸው ተከትለውህ ሲሄዱ አየሁ አለው ምንድን ናቸው? ቢለው እነዚህ በቆብ የምትወልዳቸው ንጹኃን መነኮሳት ናቸው አለው::

ሁለተኛ አመልክትልኝ አለው አመለከተለት እንዳመለከተም ፊቱ ጠቆር አለ ምነው ምን አየህ አለው በክንፋቸው ጥቁር ላባ የተቀላቀለባቸው

አየሁ አለው ምንድን ናቸው ብሎ ቢጠይቀው ጽድቅና ኃጢአት እየቀላቀሉ የሚሰሩ መነኮሳት ልጆችህ ናቸው አለው፡፡

ሦስተኛ አመልክትልኝ አለው አመለከተለት ወዲያውም ሰምቶ ጮኸ ኧለቀሰ ምነው አለው እንደቁራ የጠቆሩ ርግቦች አየሁ አለው ምንድን ናቸው አለው ሹመት ፈላጊዎች ናቸው ገንዘብ ወዳጆች ከነገሥታት ጋር በማለዳ ማዕድ የሚሰለፉ በኋላ የሚነሱ ኃጥአን መነኮሳት ናቸው አለው›› ይላል ትንቢቱ በጣም የሚገርም ቃል ነው እንደቁራ የጠቆሩ ብሎ የዛሬ የከተማ መነኮሳትን አለባበስ ሹመት ፈላጊዎች ገንዘብ ወዳጆች ከነገሥታት ጋር በማዕድ የሚሰለፉ ብሎ የዛሬ ሥራቸውን ልክ ዛሬ እንዳያቸው አድርጎ መናገሩ እነርሱ ከመነሳታቸው በፊት ትንቢቱ የተነገረላቸው መነኮሳት ነን ባዮች በከተማችን ተሰማርተው ይታያሉ ፡፡

እነዚህ መነኩሳት ዛሬ በከተማ ተሰማርተው የሚገኙት ድሮ ለጽድቅ ነው በማለት በየዋነነት የጀመሩትን የምንኩስና ዓላማና ሥርዓት ዛሬ ደግሞ በዓላማ በታቀደ ወንጀል ለሥጋ ፍላጎትና በሥጋ ፍላጎት ለሚመጣው የኃጢአት ሥራ በማመቻቸት ነው የሚመነኩሱትም ለዚሁ ዓላማ ነው እስኪ ከሚመነኩሱባቸው ምክንያቶች ጥቂቶቹን እንይ

## ምዕራፍ አምስት
## የዛሬዎቹ መነኮሳት የሚመነኩሱባቸው ምክንያቶች

### ለሥልጣን

መናኝ ሹመት መውደድ እንደሌለበት የሹመት ፍቅር ሰይጣናዊ በሽታ መሆኗን አበው በፍትሐ ነገሥት ገልጸውታል የዛሬዎቹ የሚመነኩሱት ግን ከላይ በትንቢቱ እንደተነገረላቸው ከዚህ በተቃራኒው ለሥልጣን ነው ወደፊት እንደምናየው በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ የቤተ ክርስቲያኗ የሥርዓት መጽሐፍ በሆነው በፍትሐ ነገሥት ሚስት ያገባ ጳጳስ አይሾም የሚል ትዕዛዝ ባይኖርም ምንጩ ከየት እንደሆነ ባይታወቅም ሚስት ያገባ ጳጳስ አይሾምም



መባሉ ጳጳስ ሆነው ባለሥልጣን ለመሆን መነኮስን ብለው ቆብ የሚጭኑ ጥቂት አይደሉም በዚህ ሁኔታ የመነኮሱት አንዳንዶቹ በቀላሉ ሲሳካላቸው አንዳንዶቹ ደግሞ አልሳካላቸው ሲል ተከታዮቻቸውንና የዋህን ምዕመናንን የድጋፍ ፊርማ በማስፈረም ይህን የጽጽስና ሥልጣን ለማግኘት ጥረት አድርገው እንዳልተሳካላቸው እንሰማለን፡፡

ሌላው ደግሞ የቤተ ክርስቲያን አለቃ ለመሆን ነው በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው የቤተክርስቲያን አለቃ የሚሆኑት እነዚሁ መነኩሴ ነን ባዮች ናቸው ስለሆነም ባለትዳር ከመሆን ይልቅ መነኩሴ ነኝ የሚሉት ባለሥልጣን ሆነው ዓለምን ለማጣጣም ነው ሹመት መውደድ ሰይጣናዊት በሽታ እንደሆነች ግን ከላይ ያየነው የአበው ቃል ይነግረናል በዚህ በሽታ ሰይጣን የሚያሰቃያቸውን ለማየት ደግሞ አለቅነት ሹሙን ብለው የሚንቆራጠጡትን መነኮሳት ነን ባዮች አዲስ አበባ ሀገረ ስብከትና ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሄዶ ማየትና እግዚአብሔር ይማራችሁ ማለት ይቻላል እነርሱ በሽታ መስሎ ስለማይታያቸው አሜን ላይሉ ይችሉ ይሆናል እንጂ ዞሮ ዞሮ በእነርሱ በሽታ ቤተክርስቲያን እየታወከች ስለሆነ እግዚአብሔር ይማራቸው ማለትና ለበሽታቸውም መፍትሔ መፈለግ ይገባል ወደፊት እንደምናየው ይህ ሥልጣንን የመውደድ የሰይጣን በሽታ አሳብዷአቸው ጳጳሳቱ ሳይቀሩ ነፍስ እስከማስገደል ደርሰዋል ታዲያ ይህ በሽታ የቤተክርስቲያን ጭምር በሽታ አልሆነም ይባላል?

### ትምህርት ስለማይገባቸው

ከቅኔ የትምህረት አሰጣጥ በስተቀር ሌላው ብዙም የሰውን አስተሳሰብ የሚያዳብር ባይሆንም የቤተክርስቲያናችን የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ሽምደዳ ስለሆነ ብዙዎቹ ይህ የሽምደዳ ትምሀርት አልሆንላቸው ሲልና ጓደኞቻቸው ተምረው ካህን አስተማሪ ሆነው ሲበልጧቸው ቤተክርስቲያን በማገልገላቸውም የተሻለ ጥቅም ወይም ደመወዝ ሲያገኙ ሲያዩ ካህን ለመሆን እንኳን በእኛ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ትምህርት አይጠየቅም መሪ ጌታ

ሆኖ ግን ቤተክርስቲያን በማገልገልና በማስተማር ብሎም የአብነት መምህር ለመሆን ከፍተኛ ድካምና ትጋት ስለሚጠይቅ እነዚህ ሰዎች ደግሞ ሰነፎችና ትምህርት አልገባቸው ሲል እነዚያ ጓደኞቻቸው ከደረሱበት ደረጃ ለመድረስ ብሎም ከነርሱ በላይ ባለሥልጣን ለመሆን አቋራጭ ዘዴ መነኩስን ማለትን ይመርጣሉ ።

ይህም በቆሎ ትምህርት ቤት አብረውን በነበሩ በብዙ ሰዎች እያየነው ያለ ጉዳይ ነው ብዙ ሰዎችን እንደምናያቸው ትምህርት አልገባቸው ብለው አለዚያም ጎበዝ ተማሪ ትምህርቱን ተግቶ ሲማር መንደር ለመንደር ሲያውደለድሉ የነበሩ ሁሉ በኋላ ያንን ምንም ያልያዘ ጭንቅላታቸውን በቆብ ሸፍነው መነኮስን ብለው እነዚያ ትምህርታቸውን ተምረው በሙያቸው በተሰማሩት ላይ በበላይ ሆነው ሲያቃጥሉአቸው ይኖራሉ እነርሱንም ብቻ አይደለም የቤተክርስቲያን አለቃ በሆኑበት ቦታ ሁሉ ቤተክርስቲያንን በእውቀታቸው መምራት አልሆንላቸው ሲል ሕዝብን ከሕዝብ ካህንን ከካህን ካህንን ከሕዝብ በማበጣበጥ ቤተክርስቲያን ሲያውኩ ይኖራሉ ።

በአሁኑ ሰዓት በየአንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚገኙት አገልጋዮች በትምህርት ዝቅተኛ መነኮሳት ነን ባዮች ወይም እነ አባ ዓለም በዘዴ ናቸው'የደብር አለቆችን ጨምሮ ከመቶ ዘጠና አምስት ያህሉ መነኮሳት ነን ባዮች ከሁሉም የቤተክርስቲያን አገልጋዮች በእውቀት ያነሱ ናቸው ይህንንም አብዛኛው ካህናት ቤተክርስቲያን የሚያዘወትር ምዕመን የሚያውቀው ነው አንዳንድ በትምህርታቸው ሻል ያሉ ቢኖሩ እንኳን መጀመሪያ በጥሩ ዓላማ ተነስተው መንኩሰው በኋላ አቅጣጫቸውን የሳቱ ናቸው ወይም እነርሱ ብዙ ተምረው ያልተማሩት በአቋራጭ ሥልጣን ይዘው ሲያይዋቸው ተምረው ማስተማራቸውን ትተው ወደምንኩስና የገቡ ናቸው ዞሮ ዞሮ ሁሉም ለቤተ ክርስቲያን በተሻለ አመራር ሲመሩ ወይም ሲያገለግሉ አይታዩም በትምህርት ማነስ ብቻም ሳይሆን በዓላማ መሳትም ምክንያት እስካሁን ከሀገራችን የተሾሙትን ጳጳሳት ጨምሮ በምንኩስና ማዕረግ ከነበሩም ሆነ ካሉት የማስተማሪያ ጽሑፍ እከሌ የሚባል የለም ማለት



ይቻላል በተለይ በጵጵስና ደረጃ በጽሑፍ በማስተማር ደረጃ ቤተክርስቲያኗ አልታደለችም ለማለት ያስደፍራል ለትውልድ የሚተላለፍ በጊዜውም ለሰው በሚባ ቋንቋ በሰል ያለ ጹሑፍ የጻፈ ጳጳስ አለ ለማለት ብዙም አያስደፍርም ይህም የሆነበት ምክንያት አንደኛው ምክንያት ከላይ እንዳልሁት አብዛኞቹ ወደምንኩስና የሚመጡትና እስከጵጵስና ደረጃ ድረስ ሥልጣን የሚይዙት በትምህርት ስላልሆነ ነው።

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ቀደም ብየ እንደጠቀስኩት አብዛኛው ቤተክርስቲያናችን ትምህርት በሀገራችን ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ ባይታወቅም ከጥቂት ዘመናት በፊት ጀምሮ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴው የሚጠቅመውንም የማይጠቅመውንም የቀድሞ ሰዎች የጻፉትን የተናገሩትን መሸምደድ ብቻ እንጂ ትምህርቱ የተማሪውን አዕምሮ የሚያሰፋና የሚያመራምር ስላልሆነ ተመራምሮ ለማወቅም እንደ ክህደት ስለሚቆጠር በነዚህ በሁለት ዓይነት ምክንያቶችና በሌሎችም ምክንያቶች ምንኩስና አቅጣጫውን ከመሳቱ ጋር ተዳምሮ ከመነኮሳት በተለይም ከጳጳሳት ፍሬ ያለው የማስተማሪያ መጽሐፍ መጻፍ አልተቻለም ።

በሌሎች ሀገሮች ቀድሞም የነበሩ ጳጳሳት ሃይማኖተ አበው የተባለውን መጽሐፍ ጨምሮ ሌሎችንም ድርሰቶች ጽፈው ለትውልድ አስተላልፈውልናል የዛሬዎቹም እየጻፉ ነው ምነው የእኛ ቤተ ክርስቲያን የወላድ መካን ሆነች አሁን ያለው የምንኩስናና የጵጵስና አካሄድ ወደ ተሻለ መስፈርት ካልመጣና ባለበት አካሄድ የሚቀጥል ከሆነ የወላድ መካንነቷ መፍትሄ የሚኖረው አይመስለኝም።

## ለመከበር

የሀገራችን ምዕመናን ቀደም ሲል ብዙም የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤ ስላልነበራቸው በጋብቻ ከመኖር ይልቅ በምንኩስና መኖር የበለጠ የጽድቅ አኗኗር እንደሆነ አድርገው ስለሚያምኑ በጋብቻ ከሚኖሩት ካህናት ይልቅ ለመነኮሱትና ለባህታዊ የበለጠ ክብር ይሰጣሉ ስለዚህ ነው ጸጉራቸውን

በማሳደግ አሁን አሁን ደግሞ ሰው ሰራሽ ጸጉር በመጎንጎን በየከተማው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌለው ጩኸት በሚጮኹ ባህታውያን ነን ባዮች ሥር ተሰብስቦ ፍሬ አልባ ስብከታቸውን ሲያዳምጥ የሚውለው ከዚህ ከምዕመናን የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤ ማነስ የተነሣ ከባለ ትዳር ይልቅ ለመነኩሴው የሚሰጠውን ክብር ለማግኘትና ጻድቅ ቅዱስ ለመባልና በዚያውም የሥጋ ፍላጎታቸውን ለማሳካት ወደ ምንኩስና የሚገቡ ብዙዎች ናቸው።

በምንኩስና መኖር በጋብቻ ከመኖር የበለጠ አድርገው ያስቡ እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ስናየው ግን ከጋብቻ የበለጠ አይደለም ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው የእግዚአብሔር ጸጋና ጽድቅ የሚገኘው በማግባትና ባለማግባት ሳይሆን በእግዚአብሔር ምርጫና በተመራጩ መልካም ሥራና ታዛዥነት ነው እግዚአብሔር ሰዎችን ሲመርጥ አንተ አግብተሃል አንተ አላገባህም ብሎ የመረጠበት ጊዜ የለም አብርሃምን ከሀገሩ ሲጠራው በጋብቻ ላይ እያለ ነበር ሲመጣም ሚስትህን ትተህ ውጣ አላለውም ዘጸ 2፥21 3:10 ሙሴን እስራኤልን እንዲመራ ሲመርጠው በትዳር ላይ እያለ ነበር ሲልከውም ሚስትህን ትተህ ሂድ አላለውም እንዲያውም በኋላ ሚስቱ ኢትዮጵያዊት በመሆንዋ ወንድሙ አሮንና እኅቱ ማርያም ቢያሙት እግዚአብሔር ተቆጥቶ ቀጥቷቸዋል።

‹‹እርሱ ‹በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው እኔ አፍ ለአፍ በግልጥ እናገረዋለሁ በምሳሌ አይደለም የእግዚአብሔርንም መልክ ያያል በባሪያየ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ስለምን አልፈራችሁም በማለት የርሱን ክቡርነት ነግሮአቸዋል /ዘኁ 12:1 -8 / በሐዲስ ኪዳንም ሚስት አግብቶ የነበረውን ቅዱስ ጴጥሮስን የሐዋርያት አለቃ አድርጎታል በእምነቱም‹‹ አንተ ብፁህ ነህ›› ብሎ አመስግኖታል የቤተ ክርስቲያን ሀላፊነትና የማሰርና የመፍታትም ሥልጣን ሰጥቶታል ባለትዳሮችን እንደዚህ እንደመረጠና እንዳከበረ ሁሉ ሳያገቡ የሚኖሩትንም መርጧል አክብሮአል በገዳም በብህትውና ይኖር ወደነበረው ዮሐንስ ሄዶ ተጠምቋል ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ



ዮሐንስ የሚበልጥ የለም ››ብሎ ክብሩን ተናግሮአል ማቴ 11:9 ሐዋርያው ጳውሎስንም ለወንጌል አገልግሎት የተመረጠ እቃ አድርጎታል ሐዋ 9:14 እንግዲህ የነዚህና የሌሎችንም ምርጫና ጽድቅ ስንመለከት የእግዚአብሔር ምርጫና ጸጋው የተከናወነው በማግባትና ባለማግባት ላይ አይደለም ሰዎችም የርሱን ትዕዛዝና ምርጫውን ተቀብለው በመፈጸማቸው እንጂ ጻድቅና ቅዱስ የሆኑት በማግባታቸው ባለማግባታቸው አይደለም ስለዚህ ያላገባ መነኩሴ መነኩሴ በመሆኑ ብቻ ካገባው የበለጠና ቅዱስ ነው ብሎ ማሰብ የተሳሳተ አስተሳሰብ ነው ይህ የተሳሳተ አስተሳሰብ በምዕመናን ብቻ ሳይሆን በመነኩሴ ነን ባዮች ዘንድም ያለ አስተሳሰብ ነው ለዚህም ነው ሕዝባችን መጽሐፍ ቅዱስ ካለማወቁ የተነሣ ይህን የተሳሳተ ግንዛቤ በመያዙ መነኩሴን እንደ ልዩ ጻድቅና ቅዱስ አድርጎ ስለሚቆጥር እነርሱም ቆብ በመጫን ብቻ ጻድቅ ለመባል መነኩሴ ነን የሚሉት እናም ይህን ከንቱ ሙገሳና ጻድቅ መባልን ሽተው ገብተው ወደስርቆትና ማጭበርበር የገቡት ብዙዎች ናቸው።

## ለገንዘብ

ጌታችን በወንጌል ‹‹ ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ መዝገብም/ሀብትም/ በሰማያት ታገኛለህ መጥተህም ተከተለኝ ›› ብሎ እንደተናገረው ማቴ 19:21 በሃይማኖተት አበውም መነኩሴ ከመነኮሰ በኋላ የግሉ የሆነ ገንዘብ ወርቅ ብር ሀብት ንብረት ሲኖረው እንደማይገባ ተደንግጓል አንድ ሰው ለመመንኮስ ወደገዳም ሲገባም ልጆች የሌሉት ከሆነና ንብረት ያለው ከሆነ ንብረቱን ሁሉ ለገዳሙ ማስረከብ እንዳለበት ይህን ካላደረገ ግን ዓለምን የናቀ ማናኒ መነኩሴ ሳይሆን አጋንንት የሚዘብቱበት አታላይ እንደሆነ ተጽፏል ዛሬ ግን ከዚህ በተቃራኒ መልኩ ብዙዎች መነኮስን የሚሉት በሌላ መንገድ ሊሳካላቸው ያልቻለውን የገንዘብ ማካበት በምንኩስና ስም ለማካበት ነው በሌላ መልኩ ገንዘብ ለማግኘት ለፍቶ መማር ደክሞ መሥራት ይጠይቃል ዛሬ በእኛ ቤተ-ክርስቲያን ግን ገንዘብ ለማግኘት ምንኩስና ድካም የማይጠይቅ አቋራጭ መንገድ ነው እነዚህ ለገንዘብ የተሰማሩ መነኮሳት ነን ባዮች ገንዘብ እያጋበሱ ያሉት በሁለት ዓይነት መንገድ ነው።

አንደኛው ምዕመናን ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጡትን አሥራትና መባ ጳጳስና የደብር አለቃ ሆነው በመሿሿም በስምምነት በደመወዝ በውሎ አበል በወንበር ወዘተ ስም የሚከፋፈሉት ነው በደመወዝ ብቻ እንኳን ብንመለከት የአንድ ጳጳስ ደመወዝ በአማካኝ ለስድስት ባለትዳር የቤተክርስቲያን አገልጋዮች የሚከፈለውን ደመወዝ ያህላል ይህም ለቀለባቸው ከሚወጣው ሌላ ነው የአንድ የቤተክርስቲያን አለቃ ደመወዝ ደግሞ በአማካኝ ለአራት ባለትዳሮች ደመወዝ ይሆናል በአብዛኛዎቹ በርከት ያለ ገቢ ባለባቸው አብያተ ክርስቲያናትን የሚሹሙት መነኮሳት ናቸው እንደዚህ በመስማማት በደመወዝና በሌላ በሌላ መልኩ ከሚያገኙት ገንዘብ በተጨማሪም ሙዳየ ምጽዋት እያስገለበጡ በሚዘርፉት ገንዘብ ብዙዎቹ ጳጳሳትና የደብር አለቆች አዲስ አበባ ውስጥ ዘመናዊ የሆነ ቪላ ቤታቸውን ገንብተዋል ።

ሌላኛው የገንዘብ ማግኛ ዘዴ ደግሞ እነዚህ ጳጳስና የደብር አለቃ እየተባባሉ የሚሿሿሙትና ሌሎችም ይህ እድል ያልገጠማቸውን ጨምሮ እየፈጸሙት ያለ ዘረፋ የቤተ-ክርስቲያን ማሠሪያ ለድሃ የሚመጸወት አምጣ ጸሎት እጸልይልሀለሁ ከደዌህ እፈውስሃለሁ እያሉ ጻድቅና ቅዱስ በመምሰል ለመነኩሴ ከፍተኛ አክብሮትና አመኔታ ካለው የዋህ ሕዝባችን የሚዘርፉትን ዘረፋ ነው ይህም በብዙ የዜና ማሰራጫዎች የሚሰማ ጉድ ነው ይህ የገንዘብ ማግኛ የማጭበርበር ዘዴ አሁን አሁን በጥቂቱም ቢሆን ሕዝባችን እየተማረ ሲሄድ እየነቃባቸው በመሄዱ እየቀነሰ ሄደ እንጂ ቀደም ሲል አንድ መነኩሴ ቆብ ጭኖ ከተማ ገባ ማለት ሙዳየ ምፅዋት በራሱ ተሸክሞ የመዞር ያህል ነበር ገንዘብ የሚያፍሰው ስለዚህ ነው ስርቶ ገንዘብ ማግኘት ያልቻለው ሁሉ በአቋራጭ ለመክበር ቆብ እየጫነ ወደ ከተማ የሚገባው።

## ለዝሙት

አስቀድመን እንዳየነው መነኮሳት ከተቃራኒ ጾታ ጋር መጐራበትና መተያየት መቀራረብ እንደሌለባቸው በዝሙት ድል አልነሳም ብለው የተቀራረቡ እንደሆነ እንኳን መራራቅ እንዳለባቸው ያንን ባያደርጉ ግን



ተወግዘው መለየት እንዳለባቸው በፍትሐ ነገሥት ተደንግጓል /ፍ.ነ አንቀጽ 10/

በፍትሐ ነግሥት የተደነገገው በወንጌል የተነገረውን መነሻ በማድረግ ነው ጌታችን‹‹ ስለስሜም ሚስትን የተወ መቶ እጥፍ ይቀበላል›› ብሏል ማቴ 19:29 ስለስሜ ሚስትን የተወ መቶ እጥፍ ይቀበላል ማለት ሚስት በማግባት ልጅ በመውለድ ከሚገኘው ደስታ መቶ እጥፍ የሚበልጥ ደስታ በኋላ በመንግሥተ ሰማያት ያገኛል ማለት ነው እንጂ መቶ ሚስቶች ይሰጡታል ማለት አይደለም በመንግሥተ ሰማያት ሰዎች እንደመላእክት የሚኖሩ እንጂ የሚያገቡ የሚጋቡ እንዳልሆኑ ደግሞ ራሱ ጌታ ተናግሮአል ማቴ 22፤30 ይህ ጌታችን ስለስሜም ሚስትን የተወ መቶ እጥፍ ያገኛል ብሎ የተናገረው ቃል በኋላ በመንግሥተ ሰማያት ስለሚገኝ ክብር ይሁን እንጂ የዛሬ መነኮሳት ነን ባዮች ግን በአንድ ሚስት ታሥሮ ከመኖር ይልቅ በምንኩስና ስም ከትዳር በመሸሽ ከተማ ለከተማ በመዞር መቶ ሴቶችን ማቀያየር በምንኩስና ስም አንድ ሚስት ትቶ መቶ ሴቶችን ማግኘት ብለው የተረጐሙት ይመስላል በስጋ ፍላት ሲተረጉሙት ማለት ነው።

ይህን የዝሙት ተግባራቸውን የሚፈጽሙት ደግሞ ሲመቻቸው በየቤተክርስቲያናቱ ጥግ በሚኖሩበት መኖሪያ ቤታቸው እውነተኛ መነኩሴ መስለዋቸው ከሚመጡት ወይም እንደነሱ የአመንዝራነት ስሜት ተጠናውቷቸው ፍትፍት እየተሸከሙ ከሚመጡ ባለትዳሮችና ጋለሞታዎች ጋር እንዲሁም ወላጆቻቸውን ቤተክርስቲያን ስነምግባር ይማሩልናል ብለው የሚልኳቸውን ልጃገረዶች በማባበልና አስገድዶ በመድፈር ነው በዚህም በአስገድዶ መድፈር እጅ ከፍንጅ ተይዘው የክስ መዝገባቸው ፖሊስ ጣቢያ የሚገኙ ብዙዎች ናቸው በገዳም ሳይቀር ሴቶችን በማባበል ኤድስ አስይዘው በመገናኛ ብዙኃን የሰማናቸው አሉ ይህ በቤተ-ክርስቲያን አካባቢ የሚደረገው ያልተመቻቸው ደግሞ በየ ቡና ቤቱ በመዞር ከሴተኛ አዳሪዎች ጋር ነው።

የሚያመነዝሩት በዚህ ዙሪያ በኋላ የጥቂቶችን ታሪክ እናያለን ታመው ፈውስ ፈልገው ወደ ቤተ-ክርስቲያን ከሚመጡ ሴቶች ጋር የሚያመነዝሩትም ብዙዎች ናቸው።

ጸበል እንረጫለን በመስቀል እንዳስሳለን እያሉ በዚያው አንቀው እየያዙ ተደርሶባቸው የተዋረዱ ስንቶች ናቸው እነዚህ ላይ ቆየት ያለና አንድ ዲያቆን የገጠማት የቅኔ ስንኝ ላንሳ አንዲት ወጣት ታማ ለጸበል ወደ ቤተ-ክርስቲያን ትመጣና ደጀ ሰላሙ አካባቢ ታርፋለች ከዚያ ወጣ ገባ ስትል የቤተ-ክርስቲያን አስተዳዳሪ የሆኑት መነኩሴና አንድ ዲያቆን ሁለቱም ቀልባቸው ያርፍባታል ከዚያም መነኩሴው ለመጠየቅ እያሉ በምክንያት ወደርሷ እየተመላለሱ ለርሱ እንቅፋት ይሆኑበታል ከዚያም በቅኔ፡

« ከደጀ ሰላሙ ታመሽ ተኝተሽ

እንደት እያሉ <u>አባ ባሱብሽ</u> » ብሎ ተናገረ ይባላል

ከዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባ ነገር ይህን ሁሉ በግልጥ ልናገር ተገደድሁት በምንኩስና ስም እተፈጸመ ያለውን ደባ ሕዝባችን አውቆ ራሱን ከነዚህ ዓይነት አመንዝራዎችና ሌቦች እንዲጠነቀቅና ይህ ዓይነት ሥርዓትም የእውነተኛው ምንኩስና ሥርዓት አለመሆኑን አሁን እየተፈጸመ ያለው የምንኩስና ሥርዓት አላማውን የሳተ መሆኑን እንዲያውቅ ለማድረግ ነው ወላጆችም ልጆቻቸውን ከእነዚህ ዓመንዝራዎች ሥራ ልጆቻቸውን እንዲጠብቁ በተለይ በዚህ የአስከፊ በሽታ ዘመን መጠንቀቅ እንዳለባቸው ለማስገንዘብ ነው፡፡

## በስንፍና ምክንያት

ስንፍና ለሕጉ ወጥ ምንኩስና ያደረገው አስተዋጽኦ በሁለት ዓይነት መንገድ ነው አንደኛው ከገዳም ውስጥ የነበሩት ወደ ከተማ እንዲኮበልሉ አድርጓል፡፡

ሁለተኛ ደግሞ ወደገዳም ያልገቡና ሠርቶ መብላት ሞት መስሎ የታያቸው ሁሉ ምንኩስናን የሥራ መሸሻ ምሽግ እንዲያደርጉ አድርጓቸዋል ከገዳም የሚወጡት በመጀመሪያ ወደ ገዳም ሲሄዱ በገዳም ሥራ ያለ መሆኑን ሳይረዱ ይሄዱና ከገቡ በኋላ ሠርቶ በመብላት ሳይደሰቱ ምንኩስና እስከሚቀበሉ እንደነገሩ ይቆዩና በኋላ ከመነኮሱ በኋላ ይኮበልላሉ በገዳም ያለሥራ መኖር አይቻልም ለጸሎት የተመደበው በየሰዓቱ ጸሎት ያደርሳል



ምግብ የሚያበስለው ምግብ ያበስላል ከብት የሚጠብቀው ይጠብቃል ሁሉም በየተመደበበት ይሠራል ይህን የማይወዱ ሰነፎች ግን በከተማ ዝም ብሎ አባ አባ እየተባሉ ወፍራም ደመወዝ ተከፍሏቸው ከየዋኃን ምዕመናን ፍትፍት በሳህን እየቀረበላቸው የሚበሉ መሆናቸውን ሲያውቁት ገዳሙን ጥለው ይኮበልላሉ መቼም ለጽድቅ በምንኩስና ከገዳም ወደ ከተማ እንደማይወጡ ግልጽ ነው በፍትሐ ነገሥት መነኮሳት ከገዳም ከወጡ ምንኩስናቸውን ትተው እንደሕዝብ ሆነው ይኑሩ ተብሎ ተደንግጓል ከዚህ ጓንፃር ሲታይ አሁን በከተማ እያታለሉ ያሉት መነኩሴ ነን ባዮች ሕገ ወጥ መነኮሳት አይደሉም ይባላል ወይስ ፍትሐ ነገሥት ተሳስቷል?

ይህ ቀደም ሲል ሥራ የጠሉ መነኮሳት ከገዳም እየወጡ ከተማ የተሰማሩበት ሁኔታ ነበር አሁን አሁን ግን ወደገዳም መሄዱ ሳያስፈልግ በቆሎ ትምህርት ቤት ትምህረት አልገባህ ያለውና ቢገባውም ለመማር ልቡ በስንፍና የደነዘዘው. እንዲሁም ሌላ ሥራ ሠርቶ መብላት ሞት የመሰለው ሁሉ ያለድካም የሚዘርፍበት የሰነፎች ክፍት የሥራ መደብ ወይም ቀረጥና ግብር የማይከፈልበት የንግድ ፈቃድ ስለሆነ ወደዚህ ይሰማራል መማርም መሥራትም ምጥ የሆነበት ጭንቅላቱ ይህን አማራጭ ሲያገኝ ለመወሰን ምን ገዶት እንቅፋት የሌለበት ሜዳ መስሎ ነው የሚታየው የዘመኑ ምንኩስና ማለቴ ነው እንጂ የድሮው ምንኩስና ግን የመከራ ኑሮ ነበር ለእምነት የሚከፈል መከራ ማለቴ ነው፡፡

## ከሀገር ውጪ ለመውጣት

የምንኩስና ዓላማና ስሜቱ ሳይኖራቸው ውጪ ሀገር ለመሄድ የምንኩስና ልብስ የሚለብሱም ብዙዎች ናቸው በአሁኑ ጊዜ በቤተ-ክርስቲያን በሌላው በሥልጣን በደመወዝ ከፍተኛው ድርሻ ለመነኮሳት እየተሰጠ እንዳለ ሁሉ ወደውጪ ሀገር ለመውጣትም በአብዛኛው እንዲያውም በሙሉ ማለት ይቻላል እየተፈቀደ ያለው ለመነኩሳት ነው በርካታ መነኩሳት በየጊዜው ወደ ውጪ ይሄዳሉ በዚህም የተነሣ ብዙ ሰዎች ቆብ እየጫኑ ሌላ ነገር ሳያስቡ

ዛሬ እወጣለሁ ነገ እወጣለሁ በማለት ደጅ በመጥናት ጠቅላይ ቤተ-ክህነት የሚጉላሉ ብዙዎች ናቸው። በሌላ መንገድ ለመውጣት ቢያንስ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ማጠናቀቅ ይጠይቃል እነዚህ ሰዎች ደግሞ የቤተ ክርስቲያናን ትምህርት እንኳን በደረሰበት አያድረሰኝ እያሉ ሲያውደለድሉ የኖሩ ናቸው እንኳን አሥራ ሁለተኛ ክፍል ሊያጠናቅቁ

ስለዚህ ትምህርት የማይጠይቀው መንገድ ምንኩስና ስለሆነ ምንኩስናው መርካቶም ይፈጸም አራት ኪሎ ያልተደከመበት ድግሪ ስለሆነ በቀላሉ መነኩሴ ነኝ ብሎ መቅረብ ነው ከዚያም የውጪ ሀገር እድል ይሰጠኝ ማለት ነው ከዚህ ላይ ትዝ የሚለኝ አንድ ነገር አለ አንድ ጓደኛችን ነበር በትምህርትም በሥራም በጣም ሰነፍ ነው ብቻ ከዚያም ከዚያም ብሎ በሚያገኘው ገንዘብ ሲፈልግ የሚገኘው ጠጅ ቤት ነው በኋላ ለአንድ ሳምንት ጠፍቶ ሰንብቶ መነኮስኩ ብሎ ቀሚስ ለብሶ ቆብ ጭኖ መጣ ከዚያ ለምን መነኮስክ ብለን ብንጠይወቀው ጓደኞቼ ሁሉ እየመነኮሱ ወደ ውጪ ሀገር ሲሄዱ እኔ ለምን እቀራሁ ውጪ ሀገር ለመሄድ ነው የመነኮስኩት አለን።

እነዚህ ሰዎች ይህን በማሰብ የመነኮሱትም ለሌላ ዓላማ የመነኮሱት ወደ ውጪ ሀገር የሚሄዱት በዋናነት ለሁለት ዓላማ ነው አንደኛው ለመሥራት ሰነፎች ስለሆኑ ሀገር ውስጥ ሠርተው ገንዘብ ስለማያገኙ በምንኩስና ስም በማታተልም መቼም ለሁሉ አይሳካምና ለሥልጣንም ለገንዘብም አልሳካላቸው ሲል ይህን የገንዘብ ጥማታቸውን ለመወጣት ነው ከዚያም የሚሄዱት ሠርተው ለማግኘት ሳይሆን ሰርተው ለማግኘት ተሰደው ከሄዱት ኢትዮጵያውያን በሀገር ውስት እንደሚያደርጉት ከደመወዛቸው ውጪ ለቤተክርስቲያን ማሰሪያ ለገዳማት መርጃ እያሉ ለመግፈፍ ነው የዋሁ ሕዝባችንም ለሃይማኖቱና ለሀገሩ ፍቅር ስላለው በስደት ለፍቶ ካገኘው ይሰጣል።

ሌላው ደግሞ በነጻነት ለማመንዘር ነው ብዙዎቹ መነኮሳት በሀገር ውስጥ ከገጠር ይልቅ በታላላቅ የሀገራት ከተሞች ይልቁንም አዲስ አበባ



መኖርን ይመርጣሉ ከዚህ ባለፈ ደግሞ ከሀገር ውጪ መሄድን ይናፍቃሉ ይህ ለጽድቅ እንዳልሆነ ሁሉም ያውቀዋል ታዲያ ለምን ነው ሲባል ገንዘብ ከማግኘት ጋር ለማመንዘር እንዲመቻቸው ነው።

በሀገራችን በተለይ በገጠር ምዕመናን በቅርበት ስለሚከታተሉዋቸው እውነተኞቹ መነኮሳት ካቆዩን የምንኩስና አኗር የተነሣም በነዚያኞቹ መንገድ እንዲሄዱለት ሕዝባችን ጫና ስለሚያደርግባቸው ተሰውረው ለማወናበድ ስለማያመቻቸው እነርሱም ነፃ ሆነው አይኖሩም በተላላቅ ከተሞች ግን በተለይ በአዲስ አበባ በአንዱ አካባቢ ሲያመነዝሩ አድረው ውለው በሌላው አካባቢ ጻድቅ በመምሰል ሲቀድሱ ሲያስተምሩ ሲባርኩ ይታሉ ፒያሳና አራት ኪሎ ጭፈራ ቤቶች አድረው ሃደው ጥዋት ቀድሰው የሚያቆርቡ ብዙዎች እንዳሉ ብዙዎቻችን የምናውቀው ሃቅ ነው። ያውም የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ከነዚህ ብዙዎች ገጠር አካባቢ አስገድዶ በመድፈር የወንድ ሚስት በማባለግ ሆቴል ከሴተኛ አዳሪ ጋር በማደር ተይዘው ተባረው ወደ አዲስ አበባ ገብተው የቤተክርስቲያን አለቃ ሆነው ሚኖሩ ናቸው ዛሬ በነፃነት በየጭፈራ ቤቱ ሲጨፍሩ ያድራሉ የጥቂቶችን ታሪክ በኋላ እናያለን ከሀገር ውጪ የሚሄዱትም አንዱ ዓላማቸው ይህን የዝሙት ፍላጎታቸውን በነፃነት ለመፈጸም ነው ይህ ሁሉ እነርሱን በቅርብ የሚያውቃቸው ሁሉ የሚያውቀው ሀቅ ነው።

## ለእውነተኛ የምንኩስና ዓላማ

አባ ዓለም በዘዴዎች የሚመነኩሱት በሁለት ዓይነት መንገድ ነው አንደኛው ከዚህ በላይ ለዘረዘርኳቸው ነገሮች ብለው ተዘጋጅተው የሚመነኩሱት አባ ዓለም በዘዴዎች ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ መጀመሪያ እውነተኛውን የምንኩስና ኑሮ ለመኖር አስበው ወደ ገዳም ገብተው መንኩሰው በኋላ ግን የገዳሙን ኑሮ መኖር አቅቷቸው ከገዳማቸው ወጥተው በከተማ የተሰማሩ በግብራቸው ከላይ ለተዘረዘሩት ነገሮች ብለው ከመነኮሱት ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው እንዲያውም ምንኩስና አቅጣጫውን እንዲስትና የወንበዴዎች ጭንብል

እንዲሆን በር የከፈቱ እነዚህ የገዳሙ ኑሮ አልሆንላቸው ሲል ሰይጠን ወደ ከተማ ያስኮበለላቸው መነኮሳት ናቸው በዚህ ሁኔታ ቀደም ብለው የወጡት በገንዘብ ሲበለጽጉና በሥልጣን ሲደላደሉ ሲያይዋቸው ከገዳም የነበሩት ጎረቤቱ አሜሪካን ሀገር ሄደ መክበሩን እንደሰማ ሰው ገዳማቸውን ትተው በነርሱ ግብር ተሰማሩ በከተማ በየአብያተ ክርስቲያናት ተጠልለው የኑሮ ጉዳይ ግራ ገብቷቸው የነበሩም ሚስት ማግባት አስበው የነበሩ በመተው አግብተው የነበሩ ሳይቀሩ እየፈቱ ከገዳም የወጡት ሰልጥነው በአጭር ጊዜ ሲከብሩ አይተው ለማጭበርበርማ ከነርሱ ይልቅ በከተማው የኖርንበት እኛ አንበልጥም ብለው ነው መሰለኝ ቆብና ቀሚሳቸውን ከዚሁ ከአራት ኪሎ እያሰፉ መንኩሰናል እያሉ ተሰማሩበት በአሁኑ ጊዜ ከገዳም ወደ ከተማ ከሚፈልሱት ይልቅ በማጭበርበርና በማምታታት ስልታቸው እነዚህ ከዚሁ ቆብ ገዝተው የሚጭኑት በልጠዋል ወጣት ሴቶችን ከጎናቸው አቀፍ አድርገው ሲዝናኑም ፒያሳና አራት ኪሎ አካባቢ ከምናያቸው ወጣቶች ጋር አንድ ዓይነት ናቸው የኖሩበት ስለሆነ ከገዳም እንደወጡት የማፈርና የመንከርፈፍ ሁኔታ አይታይባቸውም ይህም በቅርብ የሚያውቃቸው ሁሉ የሚመሰክረው ጉዳይ ነው በተለይ በማወቅም ባለማወቅም ለዝሙት ሥራቸው ተሳታፊ የሆኑ ሴቶች በግልጽ የሚመሰክሩት ጉዳይ ነው ባለማወቅም በማወቅም እየቀረቡ ዲቃላ እያስታቀፉአቸው ያለቀሱ ብዙ ሴቶች ስላሉ የነርሱን የማታለል ስልት ከሁሉም በላይ እነርሱ ያውቁታል።

## የነአባ ዓለም በዘዴ አለባበስ

አስቀድሞ በመጽሐፍ ቅዱስ የዮሐንስ መጥምቁን አለባበስ ከዚያም ይህን መሠረት አድርጎ በፍትሐ ነገሥት ስለመነኮሳት በተደነገገው የመነኮሳት አለባበስ ምን መምሰል እንዳለበት የተወሰነውን አይተናል ብዙ መነኮሳትም በገዳም ያንን ተከትለው እንደ ትዕዛዙ ሲፈጽሙ ኑረዋል ዛሬም በገዳማት ያ ዓይነት አለባበስ ይታያል።



በአሁን ጊዜ በከተማ የሚገኙ መነኮሳት ነን የሚሉ ዓለም በዘዴዎች ለብሰውት የሚታዩት አለባበስ ግን የምንኩስና ዓለባበስ አይደለም አለባበሱ በቀጥታ የተወሰደው ከፈሪሳውያን ነው ጌታችን በወንጌል

‹‹ ረጃጅም ልብስ ለብሰው መዞር ከሚፈልጉ በገበያም ሰላምታ በምኩራብም የከበሬታ ወንበር በምሳም የከበሬታ ሥፍራ ከሚወዱ ከጻፎች ተጠበቁ የመበለቶችን ቤት የሚበሉ ጸሎታቸውንም በማስረዘም የሚያመካኙ እነዚህ የባሰ ፍርድ ያገኛቸዋል ›› ብሎ አለባበሳቸውንና ግብዝነታቸውን ከነማታለያ ዘዴአቸው ተናግሮአል ሉቃ 20፡ 41-47 የዛሬዎቹ ከዚህ የተለዩ ከሆኑ ያየ ሁሉ ይታዘብ እነርሱ ግን መቼም ምዕመናን አያውቁም ብለው የለበስነው የምንኩስና ልብስ ነው እያሉ ያታልላሉ ለነገሩ ይህንንም ህዝብ ፊት ለመከበሪያ የሚጠቀሙበት ስለሆነ እንደዚህ ሆነው የሚታዩት በሕዝብ ፊት ነው እንጂ ከዚያ ውጪ ግን ብዙዎች ቁምጣ ነው የሚለብሱት ሰው በማያያቸው ቦታ ሙሉ ኮትና ሱሪ ለብሰው ለብቻቸው በቤት ውስጥ የሚደሰቱም ብዙዎች ናቸው። እንደምንኩስና ሕግ ከሆነ ግን የምንኩስና ልብስ የሚወልቀው በጋ የተለበሰው ክረምት ሲገባ ክረምት የተለበሰው በጋ ሲገባ ብቻ ነው የነዚህ ግን የሚለበሰው ለመከበሪያና ለዝነጣ ስለሆነ ይህን ሕግ አይመለከትም ቀን በሕዝብ ፊት የምንኩስና የሚባለውን ለብሰው ውለው ማታ በሱፍ መዘነጥ ነው።

እርግጥ ከምንኩስና ሥርዓት አንፃር ሲታይ ማወናበጃ መሆኑ ያሳዝናል እንጂ ጽድቅ በአለባበስ የሚለካ ሆኖ አይደለም ጌታችንም ለማታለያ ስለሚጠቀሙበት ነው የነቀፋቸው ስራቸውም እንደአለባበሳቸው ስላልሆነ ነው ሕዝባችንም እየተታለለ ያለው ጽድቅን በአለባበስ እየመዘነ ሥራቸው እንደ አለባበሳቸው እየመሰለው ነው።

# ምዕራፍ ስድስት

## በምንኩስና እየተፈጸሙ ያሉ ውንብድናዎች

ከላይ ባየናቸው ሁኔታዎች ምንኩስና አቅጣጫውን በመሳቱ የተነሳ በየከተማው በምንኩስና ስም እየተፈጸሙ ያሉ በርካታ ውንብድናዎች አሉ አብዛኛዎቹም ሕዝባችን የሚያውቃቸው ናቸው::

ሆቴል ውስጥ ከሴተኛ አዳሪ ጋር አድረው ማለዳ ቤተ-ክርስቲያን መጥተው የሚቀድሱ ፒያሳና አራት ኪሎ ካዛንቺስ ጭፍራ ቤቶች አድረው ጠዋት ቤተ-ክርስቲያን ገብተው የሚቀድሱ ቀዳሾችና የደብር አስተዳዳሪዎች መነኮሳት ብዙዎች ናቸው ::ይህ ሁሉ ብዙኃኑ የአዲስ አበባ ሕዝብ የሚያውቀው ጉዳይ ነው:: አሁን አሁን ደግሞ ለገንዘብ ሲሉ እየሰለሙ ቆባቸውንና የያዙትን መስቀል ለሙስሊሞች እያስረከቡ በቆባቸው ምትክ የእስላም ኮፍያ የሚያደርጉ እየበረከቱ መጥተዋል አንዳንዶቹም ከዚያ ተመልሰው በቤተ-ክርስቲያን የሚቀድሱ አሉ:: እስኪ እኔ ከማውቀው ትንሽ ልጥቀስ

## ከምንኩስና ወደ እስልምና

በእስልምና ሃይማኖት መሪዎችና መነኩሴ ነን ባዮች ቤተክርስቲያን ሲቀድሱ በኖሩ ሰዎች በዚህ በአዲስ አበባ ከተማ የክርስትናን ሃይማኖት የሚያንቋሽሽና የሚያራክስ ድርጊት ተፈጽሟል መነኩሴ ነበርን ባዮቹ እንደሚሉት በምንኩስና በቀዳሽነት በቤተ-ክርስቲያን አስተዳዳሪነት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ከ20 ዓመት በላይ ያገለገሉ ናቸው:: አባባላቸው እውነት መሆኑን ታሪካቸው አረጋግጧል እነዚህ መነኮሳት እስልምናን ተቀብለናል በማለት ቆባቸውንና መስቀላቸውን ቀሚሳቸውን ለሙስሊም ሃይማኖት መሪዎች በማስረከብ በቆቡ ፋንታ የእስልምና ኮፍያ በሙስሊሞች ሲደረግላቸው የደረሰኝ የምስልና የድምጽ ማስረጃ ያሳያል ጥቂቶችን በፎቶ መልክ እንደሚከተለው አቀርቤአቸዋለሁ::





ኢየሱስ ክርስቶስንና የክርስትና ሃይማኖትን ከሙስሊሞች ጋር በጥያቄና መልስ መልክ በማጥላላት ላይ እንዳሉ



ክርስትናቸውን ከደው እስልምናን ሲቀበሉ



ከሰለሙ በኋላ በደስታ ከሙስሊሞች ጋር ሲሳሳሙ



ከሰለሙ በኋላ የእጃቸውንና የአንገታቸውን መስቀል ለሙሲልሞች ሲያስረክቡ





ቆባቸውን አስረክበው የሙስሊም ኮፍያ በሙሲሊሞች ሲደረግላቸው



ቆባቸውንና መስቀላቸውን ካስረከቡ በኋላ ከሙሲልሞች ጋረ አብረው ሲጸልዩ



ሙሉ የሙስሊም መለያ ልብስ እንደለበሱ ከሙሲልች ጋር ቆመው



ሙሲልሞች ከአንገታቸውና ከእጃቸው ተረክበው የወሰዱት መስቀል



ይህ ድርጊት በሚፈጸም ጊዜ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም የክርስትና ሃይማኖቶች የሚያንቋሽሹና የሚያራክሱ በርካታ ቃላት ከነዚህ መነኮሳት ነን ባዮችና በተለይም ከሙስሊም የሃይማኖት አስተማሪዎች ተነግረዋል።
ጥቂቶችን ለመጥቀስም

- ኢየሱስ ከኃጢአት አያድንም
- ኢየሱስ ፈጣሪ አይደለም
- ኢየሱስ እስላም ነው።
- መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ቃል ሰዎች የፈጠሩት የውሸት ቃል ነው።
- መጽሐፉም ከውስጡ በውሸት የተበረዘ ነው።
- በምድር ላይ ያለው እውነተኛ ሃይማኖት እስልምና ብቻ እንጂ ሌላው የውሸት ነው።
- እነዚህ ሰዎች (መነኮሳቱን ማለት ነው) ቆሞሶች ናቸው ለጵጵስና አንድ ደረጃ የቀራቸው ናቸው። ነገር ግን የያዙት ሃይማኖት ውሸት ስለሆነ እስልምናን አመኑ እያሉ የእስልምና የሃይማኖት መሪዎች ይናገሩ ነበር። ማንም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት መከተል ነፃነት ቢኖረውም የሌላውን ሃይማኖትና ተከታዮቹን መንቀፍና ማጥላላት ግን ተገቢ አለመሆኑ ሊሠመርበት ይገባዋል።

እነዚህ ሰዎች ለሰነዘሯቸው ሃይማኖታችንን የማንቋሸሽ ቃላት መልስ መስጠት የሚያዳግት አይደለም ነገር ግን እነርሱ ይህን ድርጊት የፈጸሙት እንደዚህ ያሉ ሰዎች አሰለምን ብለው ከአረብ ሀገሮች ገንዘብ ለማግኘትና ዋናው ዓላማቸው ደግሞ በእስልምናና በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ግጭት ለመፍጠር ነው። እናም ለነዚህ ሰዎች መልስ መስጠት የሚያዳግት ባይሆንም ቅድሚያውን ለሰላም በመስጠት የሃይማኖቱ መሪዎች ድርጊቱን የፈጸሙትን ግለሰቦች ይቅርታ እንዲጠይቁ እንዲያደርጉ መንግሥትም ድርጊቱ በሁለቱ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ግጭት ለመፍጠር የተፈጸመ ስለሆነ ሰዎቹን በሕግ እንዲጠይቃቸው ስል ቅድሚያውን ለሰላም እሰጣለሁ ይህ ካልሆነ ግን በሃይማኖታችን ላይ ለተደረገው ማንቋሸሽና ነቀፋ ተገቢውን መልስ ለመስጠት እንደምገደድ ለመጠቆም እወዳለሁ።

በተለይ ሰዎች ምንም ያልተማሩ ቢሆኑም ራሳቸው ብቻ ሂደው እምነቱን መቀበል ሲችሉ የእምነታችን መለያ የሆነውን መስቀል በእንደዚህ ያለ ድርጊት ከእጃቸው ተቀብለውና ካንገታቸው አውልቀው መጣላቸውና የራሳቸውን መለያ ማድረጋቸው በዝምታ የሚታለፍ-አይደለም።

## ከምንኩስና ወደ እስልምና ከእስልምና ወደ ምንኩስና

በአንድ ወቅት በነበርኩበት ክፍለ ሀገር አንድ መነኩሴ ቤተ-ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ማደሪያ ስጡኝ ብሎ እንግድነት ጠየቀ በጠየቀው መሠረትም በቤተ-ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ቤት ተሰጥቶት ተቀምጦ እያለ የቤተ-ክርስቲያን ትምህርት የተማረ ስለሆነ ቅዳሴ ልቀድስ ብሎ ጠየቀ በጠየቀውም ጥያቄ ተፈቅዶለት እየቀደሰ ምዕመናን እናቶች በአገልግሎት ላይ ስላዩት ፍትፍት በሳህን እያመጡ እየቀለቡት ለተወሰነ ሳምንታት ከቆየ በኋላ አንድ ቀን በአንድ ትልቅ ሆቴል ገብቶ የምንኩስና ልብሱን እንደለበሰ ከሴተኛ አዳሪ ጋር አልጋ ቤት ገብቶ ይተኛል በዚህን ጊዜ የሆቴሉ ባለቤት ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ሲቀድስ አይተውት ስለነበር ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በመተባበር ለፖሊስ ጠቁመው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄዶ ይታሠራል በነጋውም ቀድሞ ግንኙነት ያላቸው ኑሮ የሙስሊም መሪዎች ዋስ ሆነው ያስፈቱትና መስጊዳቸው ወስደው የቤተ-ክርስቲያን ቅዳሴ ስለተማረ ጥሩ ድምጽ ስለነበረው አዛን (የእስልምና የፀሎት ጥሪ) የሚጮህላቸው ያደርጉታል ትንሽ እንደቆየም ወደ አዲስ አበባ ይመጣና እንደገና መነኩሴ ነኝ ብሎ በአዲስ አበባ አድባራት ሲዘዋወር አዲስ አበባ በመጣሁበት ጊዜ አገኘሁት አንዳንዶቹ እንደሚሉት ደግሞ በቀዳሽነት ተቀጥሮ ሲሠራ ነበር ብለውኛል።

### ሆቴል ውስጥ ከሴተኛ አዳሪ ጋር ተደባድቦ የተባረረው የደብር አለቃ

በዚያችው ቤተ-ክርስቲያን ከላይ ያየነው ታሪክ በተፈጸመበት ወቅት የነበረው የቤተ-ክርስቲያን አስተዳዳሪ የነበረው ሌላው መነኩሴ ያችኑ ቤተ-ክርስቲያን እየበጠበጠና ቤተ-ክርስቲያን የሚመጡትን ወጣት ሴቶች እያባበለ በመድፈር ተከሶ ስላስቸገረ ምናልባት ቢሻለው ተብሎ ወደ ሌላ ቤተ-ክርስቲያን ለጊዜው ተዛውሮ እንዲቆይ ተደረገ በዚያው በተዛወረበት ቦታም ሆቴል ውስጥ ገብቶ ባንኮኒ ተደግፎ ሲጠጣ ለዝሙት ከጠየቃት ሴተኛ አዳሪ ጋር ተጣልቶ በጠርሙስ ጭንቅላቱን ፈንክታው በዚህም ምክንያት የሀገረ ስብከቱ ጳጳስ አባረውት አዲስ አበባ መጣ ዛሬ ይህ ሰው በአዲስ አበባ አድባራት በአለቅነት እየተዘዋወረ ይሠራል የሚዘዋወረውም በተመሳሳይ ድርጊት እየተከሰሰ ነው ለዚህም ዶክመንቱ በየ አድባራቱ ይገኛል በየጭፈራ



ቤቶች ከሚያድሩት የቤተ-ክርስቲያን አለቆችም አንዱ ይህ ሰው ነው የሚገርመው ደግሞ ከላይ በጠቀስኩት ታሪክ ሙስሊሞች ዋስ ሆነው ያስፈቱት፣ መነኩሴ በታሠረ ጊዜ አንዱ ከሳሽ እርሱ ነበር። ይህ ሁሉ የሚያሳየን ምንኩስና ምን ያህል የወንበዴዎችና የሌቦች ጭንብል መሆኑን ነው። ገንዘብና የሌላውን የቤተ-ክርስቲያን ንብረት ዘረፋስ መቼም ቆጥሮ መጨረስ አይቻልም።

ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ በላይ ያየናቸውን መጥቀሴ የእነርሱን ኃጢአት በመዘርዘር ጽድቅ ለማግኘት ወይም ለነርሱ የግል ጥላቻ ኖሮኝ አይደለም። በምንኩስና ስም እንደነዚህ ያሉ ሌቦችና ወንበዴዎች እየበረከቱ ስለመጡ ምዕመናን ራሳቸውን እንዲጠብቁና ቤተ-ክርስቲያንንም እንዲጠብቁ ለማድረግ ነው። በመግቢያዬ ላይ እንደገለጽኩት ጌታችን የጸሐፍትና የፈሪሳውያንን የኃጢአት ሥራ ዘርዝሮ መናገሩ ሕዝቡንና ደቀ መዛሙርቱን ለማስጠንቀቅ ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስም በተመሳሳይ ሁኔታ ተናግሯል። /ማቴ 23፥13-36፤ ሉቃ 20፥26፤ ሮሜ 2፥17-29/

## ምዕራፍ ሰባት
## ጵጵስናና መሰረቱ በመጽሐፍ ቅዱስ

ጳጳስ ማለት በግሪኩ ኤጲስ ቆጶስ የሚለው ሲሆን ትርጉሙም ጠባቂ ተቆጣጣሪ ማለት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶሳት የሚላቸው የቤተ-ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ነው። ለቲቶ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የቤተ-ክርስቲያን ኃላፊ ሽማግሌ መሾም ያለበት እንዴት ዓይነት ሰው እንደሆነ ከነገረው በኋላ ያንኑ ተሿሚ ሽማግሌ ኤጲስ ቆጶስ ብሎታል /ቲቶ 1፥5-8/ የኤፌሶን የቤተ-ክርስቲያን ሽማግሌዎችንም ጳጳሳት ብሏቸዋል /የሐዋ 20፥17-29/።

ከሐዋርያት በኋላ ክርስትና እየተስፋፋ ክርስቲያኖች እየበዙ ሲሄዱ ግን ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ የተለየ ማዕረግ እየሆነ ሄደ ከሐዋርያት ቀጥለው ከተነሱት አበው ጀምሮ ማለት ነው። ዞሮ ዞሮ የቤተ-ክርስቲያን ጠባቂ ተቆጣጣሪ አስተዳዳሪ ማለት ነው።

እንዲቀደሱ የጌታን ነገር ያስባሉ የተጋባች ግን ባሏን እንዴት ደስ እንደምታሰኘው የዓለምን ነገር ታስባለች» በማለት ከዚህ ዓለም ፍቅር ይልቅ የጌታን ፍቅር የበለጠ ለማጽናት ያለጋብቻ መኖር እንደሚቻል ተናግሮ በተጨማሪም ያገባ መልካም አደረገ ያላገባም የተሻለ አደረገ በማለት ስለማግባትና አለማግባት የተጠየቀውን ጥያቄ ደምድሟል /1ቆሮ 7፥32-38/::

ይህን ጥቅስ ከዚህ በላይ የጠቀስኩት ያለምክንያት አይደለም ባለትዳር ጳጳስ አይሾምም ብለው የሚሉ ሰዎች ባፋቸው አይናገሩት እንጂ ባለትዳር አይሾም የሚሉት በውስጣቸው ካለው ጋብቻን የመናቅ ስሜት የሚመነጭ ቢሆንም ለማታለያነት ሐዋርያው ጌታን ለማስደሰት ካገባ ያላገባ ይሻላል ብሎ ስለተናገረ ነው ይላሉ ነገር ግን የሐዋርያው ምክር እነርሱ ከሚሉት ጋር አይገናኝም የማይገናኘውም

አንደኛ እርሱም እንደተናገረው ስለማግባት አለማግባት ተጠይቆ የሰጠው ምክር እንጂ ትዕዛዝ ወይም ሥርዓት አይደለም::

ሁለተኛ ምክሩን የሰጠው በትዳር አጋራቸው ፍቅር ልቦናቸው ሳይከፈል በጌታ ፍቅር ብቻ ተጠምደው መኖር ለሚፈልጉ በድንግልና ለሚኖሩ ምዕመናን እንጂ ከጵጵስና ሹመት ጋር ምንም አያገናኘውም ለምዕመናን ሁሉ እንደሆነም ምክሩን ለሴትም ለወንድም አድርጐ ነው የተናገረው ከጵጵስና ሹመት ጋር የተያያዘ ቢሆን ኖሮ ሴቲቱንም አያጠቃልልም ነበር::

ስለዚህ ይህ ጥቅስ ያገባ ጳጳስ አይሾምም ከሚሉት የተሳሳተ ሐሳብ ጋር በምንም አይገናኝም ያውስ ቢሆን ያላገባ የተሻለ አደረገ የሚለው ቃል መሾም ያለበት መብቱ የተሰጠው ለባለትዳር ቢሆንም ያላገባም መሾም እንደ አለበት ትንሽ መከራከሪያ ይሆን እንደሆነ እንጂ የተገላቢጦሽ ባለትዳር አይሾም ሊያስብል ይችላልን? ይህ ዓይን ያወጣ ድፍረት ነው::

ይህ ዓይነት ሥርዓትና ትምህርት ቤተ-ክርስቲያኗ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትዕዛዝ ውጪ የምትመራ ናት ያስብላታል መጽሐፍ ቅዱስ ጳጳስ መሾም ያለበት ባለትዳር ነው እያለ በተቃራኒ ባለትዳር መሾም የለበትም ብሎ ተቃራኒ ሥርዓት ማውጣት ከመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ ውጪ አይደለም ብሎ የሚያስብ ካለ የክርስትና የመመሪያ መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ያላወቀ ወይም እያወቀ እንደነርሱ መቀበል ያልፈለገ መሆኑ የታወቀ ነው::



ስለዚህ ቤተ-ክርስቲያኗ የምትመራው በመጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ ይህንን በግልጽ የተቀመጠ የመጽሐፍ ቅዱስ ትዕዛዝ መቀበል አለባት አለዚያ መጽሐፍ ቅዱሱን የምትቀበለው ሙሉ ትዕዛዙን ሳይሆን የሚመቻትን እየመረጠች ነው ማለት ነው::

## የጳጳስ የሹመት መስፈርት በፍትሐ ነገሥት

ፍትሐ ነገሥትም ቢሆን ከላይ ያየነውን ሐዋርያው ጳውሎስ ያገባ ኤጲስ ቆጶስነት ይሾም ያለውን መስፈርት አልተቃወመውም በፍትሐ ነገሥት ስለ ጳጳሳት ሹመት በተደነገገው ክፍል ላይ ጳጳሳት ከሁለት ወገን መሾም አለባቸው ይላል ይኸውም:- አንደኛው ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳዘዘው ያንኑ የሐዋርያውን ቃል በቀጥታ በመጥቀስ የአንዲት ሚስት ባልና ልጆቹን በአግባቡ ማስተዳደር የቻለ እንዲሆን ያዝዛል::

ሁለተኛው ደግሞ ከመነኩሳት ወገን በክህነት ሲያገለግል የኖረ ይሾም ይላል ይህ ሁለተኛው አባባል ሐዋርያው ጳውሎስ ካስቀመጠው መስፈርት ጋር የሚቃረን ቢመስልም ከሐዋርያነት አንፃር ሲታይ የሚጋጭ አይደለም ሐዋርያው ጳውሎስ ያገባ ብቻ እንዲሾም ያዘዘው ከቤተ-ክርስቲያን አስተዳዳሪነት አንፃር ነው የሐዋርያነትና አስተዳዳሪነት ልዩነት እንዴት ነው ብሎ ለሚጠይቅ ሐዋርያነት በይበልጥ የሚያተኩረው በየሀገሩ እየዞሩ ያላመኑትን በማሳመን አምነው በእምነት ያልዳኑትን በእምነታቸው እንዲድኑ በማድረግ ሰዎችን የእግዚአብሔር ቤተሰቦች የማድረግ ሥራ ነው::

የቤተ-ክርስቲያን አስተዳዳሪነት ደግሞ የሐዋርያነት ሥራ ያለበት ቢሆንም በዋናነት የሚያተኩረው በአንድ አካባቢ የሚኖሩትን ክርስቲያኖች የአምልኮ ሥርዓት በማስያዝ በማቁረብ ሲጣሉ በማስታረቅ ከሌሎች አምልኮቶች እንዲጠነቀቁ በእምነታቸው እንዲጸኑ በማድረግ የቤተሰባዊ እንክብካቤና ጥበቃ ወይም እረኛ በጐቹን እንደሚጠብቅ ዓይነት ለምዕመናን የቅርብ እንክብካቤና ክትትል በማድረግ የሚከናወን ሥራ ነው:: ሐዋርያነት የግድ በአንድ ቦታ ብቻ መወሰን የማይጠይቅ ሲሆን አስተዳዳሪነት ግን ምዕመናንን ለመንከባከብ በአንድ ቦታ መወሰን ግድ ይላል እናም ከዚህ አንፃር ሐዋርያው ከአስተዳዳሪነት አንፃር የምዕመናንን የአኗኗር ዘይቤ አውቆ

በቤተሰብአዊ እንክብካቤ ችግራቸውን ተረድቶ እንደልጆች አድርጐ ያዝንላቸውና ይንከባከባቸው ዘንድ ሚስትና ልጆች ያሉት ይሁን አለ ይህም ያላገባና ልጆች የሌሉት ቢሾም በሚስትና በልጆቹ ያላየው ስለሆነ ለምዕመናን የማያዝን በላያቸው ላይ የከበደ ሸክም ቀንበር የሚጭን ይሆናል በማለት ነው እንጂ ያላገባ ቢሾም ክርስትናን ያረክሳል ብሎ አይደለም ዛሬ የእኛ ቤተ-ክርስቲያን መሪዎች ለሕዝብ አዘኔታና ርኅራኄ የሌላቸው በልጅና በሚስት የሚደርስውን ቤተሰባዊ ችግር ስለማያውቁት ነው ይህም ምስክር የሚያሻው ጉዳይ ሳይሆን በግልጽ እየታየ ያለ ሐቅ ነው።

እና ወደ ነገሬ ልመለስና በፍትሐ ነገሥት መነኩሴ እንዲሾም መፈቀዱ ከላይ ባየነው መሠረት ከሐዋርያነት አንፃር ሲታይ ከሐዋርያው ጳውሎስ ቃል ጋር የሚቃረን አይሆንም ለሐዋርያነት አገልግሎት ቆራጥ ዓላማ ያለው ከተገኘ ከወንጌል አንፃር ተገቢ ሹመት ይሆናል። ጌታ ሐዋርያትን ሲመርጥ ካገቡትም ካላገቡትም ነው የመረጠው ስለዚህ ያላገባ ቢሾም ከፍትሐ ነገሥቱ ላይ ያለው ቃል ስህተት ነው ሊያስኝ አይችልም ችግሩ አስቀድሜ እንዳልሁት «ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል» እንዲሉ አበው ይህንኑ እንደ አማራጭ ያቀረቡትን የፍትሐ ነገሥት ቃል በመጠቀም እነ አባ ዓለም በዘዴ ጭራሹንም ባለትዳር ጳጳስ መሾም የለበትም ብለው የጵጵስናን ማዕረግ ለምዕመናን ርህራኄ የሌላቺው የነፍስ ገዳዮች ዋሻ አደረጉት።

በዘመነ አበውም ባለትዳር ጳጳሳት ነበሩ ለምሣሌ ጎርጎሪዮስ ዘኑሲስ ባለትዳር የነበረና የጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ አባት ነው።

## በጵጵስና ማዕረግ የተፈጸመ የግድያ ወንጀል

ቀደም ሲል ከጵጵስና በታች ያለውን የምንኩስና ደባ ውንብድናና ክህደት አይተናል አሁን ደግሞ በጵጵስና ማዕረግ ከተፈጸሙት የምንኩስና ወንጀሎች አንዱን እንይ በደርግ ዘመነ መንግሥት ብዙ ኢትዮጵያውያን ደማቸው እንደፈሰሰና በዘግናኝ አገዳደል ሕይወታቸው በሜዳ ላይ እንደቀረ ታሪክ የማይረሳው ጠባሳ ነው በዚህ ዘግናኝ ድርጊት ቀይ ሽብርና ነጭ ሽብር በተሰኘ ው ዘመቻ ብቻ ያለቁት ወገኖቻችን ስድስት ሺህ እንደሚደርሱ የታሪክ መዛግብት ያመለክታሉ በዚህ ዘግናኝ ድርጊት ቤተ-ክርስቲያንን በመምራት ላይ የነበሩ ጳጳሳትም ከደርግ ጋር በመተባበር የራሳቸውንና የቤተ-ክርስቲያኗን



የነፍስ ገዳይነት ታሪክ አስቀምጠዋል ወታደራዊ መንግሥት ደርግም አትግደል ብለው ማውገዝ የሚጠበቅባቸው የሃይማኖት አባቶች ራሳቸው ሃይማኖታዊ የቀይ ሽብር የግድያ አራማጆች ሆነው ሲያገኛቸው ግድያውን ያለሥጋት ፈጸመ ታሪኩ እንዲህ ነው ንጉሡ ከሥልጣናቸው በወረዱ ጊዜ የነበሩትን ፓትርያርክ አቡነ ቴዎፍሎስን ከበታቾቻቸው የነበሩና ሥልጣናቸውን ለመያዝ ይፈልጉ የነበሩ ጳጳሳት ለደርግ መንግሥት በቂ ድጋፍ በመስጠት አሳሰሩዋቸው ከዚያም አስገደሉዋቸው ከተገደሉ በኋላ በተፈጸመው ግድያ በመደሰት ይጓጉለት ለነበረው ሥልጣን ለመብቃት በእርሳቸው ቦታ ለመተካት ምርጫ እንዲካሄድ የሚጠይቅና ግድያውን የሚደግፉ የሚከተለውን መግለጫ አወጡ ፦

ቁጥር 418/68<br>
የካቲት 18ቀን 1988 ዓ/ም

## <u>ከቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጠ</u><br><u>መግለጫ</u>

ሁሉን መሥራት የሚቻለውን አምላክ አስቀድመን እናመሰግናለን።

1. ቤተ-ክርስቲያኖችን በመንፈሳዊ ዓላማዋ ጸንታ፣አስተዳደሯን አሻሽላ፣በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ መመሪያ ተጠብቃ፣በአበው ሐዋርያት ሕግና ሥርዓት ቃለ ወንጌልን እያስተማረች፣ሕዝበ ክርስቲያን በምድራዊና በሰማያዊ ኑሮው በሥራ እንዲበለጽግ በመሠረታዊ ትምህርቷ እየመገበች፣ ራሷን በራሷ ለመምራት እንድትበቃ የኅብረተ ሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ስለቤተ-ክርስቲያን ሲል በቀድሞው ፓትርያርክ በአቡነ ቴዎፍሎስ ላይ የወሰደውን እርምጃ ደግፈናል።
2. ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ የትግራይ ሊቀ ጳጳስ ተጠባባቂ ፓትርያርክ እንዲሆኑ መወሰኑን
3. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ጊዜያዊ ጉባዔ የቤተ-ክርስቲያን ደጋፊ ስለሆነ፣ስለቤተ-ክርስቲያን ተሐድሶ አስፈላጊ የሆኑትን ጉዳዮች ሁሉ እያጠና እንዲያስፈጽም መቋቋሙን ተቀብለናል።
4. ስለአዲሱ ፓትርያርክ ምርጫ የተወሰነው ጊዜ ሳይተላለፍ በጊዜው እንዲፈጸም እንገልጻለን።

ኢትዮጵያ ትቅደም

ይህን መግለጫ ያወጡት ገና በእሥር ላይ እያሉ ነው። «የተወሰደውን እርምጃ ደግፈናል» ያሉት እንዲገደሉ ድጋፍ ለመስጠት ነው የሚሉ አሉ ያም ሆነ ይህ የተገደሉት በእነርሱ አሳልፎ ሰጭነትና ድጋፍ ነው። መግለጫውን ከነፊርማቸው ኮፒ አድርጌ አብሬ አያይዠዋለሁ ።



በጳጳሳቱ ድጋፍ ደርግ የገደላቸው የቀድሞ ፖትርያርክ አቡነ ቴዎፍሎስ



ከእነዚህ ጳጳሳት የተወሰኑት ራሳቸው አቡነ ቴዎፍሎስ የሾሟቸው ናቸው:: በዚህም መምህሩን ካስገደለው ከይሁዳ ጋር ይመሳሰላሉ ይሁዳ ከካህናት ፣አለቆች ክርስቶስን ለማስያዝ ገንዘብ ከተቀበለ በኋላ የነበረውን ሐሳቡን «ከዚያችም ሰዓት ጀምሮ አሳልፎ ለመስጠት ምቹ ጊዜ ይሻ ነበር» በማለት ወንጌላዊው መዝግቧል /ማቴ26÷16/ ይሁዳ የገንዘብ ፍቅር በልቡ ስላደረበት ገንዘቡን ተቀብሎ ምቹ ጊዜ ፈልጎ መምህሩን ለገዳዮቹ አሳልፎ ሰጠ እነዚህም የሹመት ፍቅር በልቦናቸው ስላደረ ሳይሳካላቸው የቆየ በመሆኑ ምቹ ጊዜ ሲያገኙ አባታቸውንና መምህራቸውን ለገዳዩ የደርግ መንግሥት አሳልፈው ሰጡ አሁን እነዚህ ከይሁዳ የሚለዩበት ምን ነገር አለ?

እነዚህ ሰዎች ክርስቶስን ቢያገኙት አይገድሉትም ብሎ ማሰብ ይቻላልን? እኔ በበኩሌ አይገድሉትም ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው የሚመስለኝ:: በፍትሐ ነገሥት «ሹመትን መፈለግ ሰይጣናዊት በሽታ ናት»ተብሎ እንደተጻፈው በዚች ሰይጣናዊት በሽታ ስለተጠመዱ ክርስቶስንም ቢያገኙት አይተውትም ነፍስ ገዳዮች የሰይጣን ልጆች እንደሆኑ ደግሞ ጌታችን ልክ እንደነዚህ ያሉ ነፍስ ገዳዮች ሊገድሉት እንደሚፈልጉ ባወቀ ጊዜ «እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ እርሱ ከመጀመሪያ ነፍስ ገዳይ ነበረ» ብሎ የነዚህን የሰይጣን ልጅነት አስቀድመው በነበሩት ነፍስ ገዳዮች ሥራ ተናግሮታል:: /ዮሐ 8÷44/ እና እነዚያ አስቀድመው ባይገድሉትና በነዚህ ጊዜ እዚህ ቢገኝ ኑሮ እነዚህ ይገድሉት ነበር:: ጌታ እንዳለውም የሚሾፍራቸው ሰይጣን ስለሆነ እርሱ እንደሆነ በየዘመኑ ሥራ ማሠራት ያውቅበታል:: በነዚያ አድሮ ጌታን አስገደለ በነዚህ አድሮ ደግሞ አቡነ ቴዎፍሎስን አስገደለ በአቡነ ቴዎፍሎስ ቦታ ጌታ ቢገኝ አያስገድሉትም ብሎ ማሰብ ሞኝነት ይሆናል::

ከነዚህ ነፍስ ገዳዮች የተወሰኑት በመኪና አደጋ ሞቱ በቀጥታ የፈረሙት ብቻ ሳይሆኑ የውስጥ አዋቂዎች እንደሚሉት በመኪና አደጋ ከሞቱት ጳጳሳት አብዛኞቹ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በነፍስ ግድያው የተሳተፉ ናቸው:: ነገሩ ግን ለሕዝባችን እንቆቅልሽ ሆኖ ቆይቷል::

በመግለጫው ላይ እንደሚታየው እነዚህ ጳጳሳት ቤተ-ክርስቲያኗን ወክለው የቤተ-ክርስቲያኗ ውሳኔ ነው ብለው ነው የሲኖዶስ መግለጫ በማለት

መግለጫውን ያወጡት ስለዚህ እነርሱ ብቻ ሳይሆኑ ቤተ-ክርስቲያኗን ነፍሰ ገዳይ አድርገዋታል።

በውኑ ቤተ-ክርስቲያን በእንደነዚህ ያሉ ነፍሰ ገዳዮች መመራቷ አያሳዝንምን? እንዲህ ያሉ ነፍሰ ገዳዮች ቀድሰው ሰው ባስገደሉበት እጃቸው ቅዱስ ቁርባንን ቆርሰው ማቀበላቸው አያሳዝንምን?

ምዕመናን ከእነዚህ ነፍሰ ገዳዮች በረከት እናገኛለን ብለው ጫማቸውን እየሳሙ መስገዳቸው አያሳዝንምን?

እነዚህ ነፍሰ ገዳዮች ቤተ-ክርስቲያን መድረክ ላይ ቆመው አትግደል ብለው ማስተማራቸው አያሳፍርምን?

ቤተ-ክርስቲያን የወንበዴዎችና የነፍሰ ገዳዮች ዋሻ መሆኗ ምንኩስናም እንደዚህ- ያሉ የነፍሰ ገዳዮች ጭንብል መሆኑ በዚች ሐዋርያዊት ቤተ-ክርስቲያን እምነት ለምንኖር ታላቅ ሐፍረት ነው ይህን አሳፋሪ ድርጊት ለሕዝብ ማጋለጡ ለምን ይጠቅማል? የሚል ስሜት በብዙዎቹ ዘንድ እንደሚፈጠር አውቃለሁ ነገር ግን አንድ የተበላሸ ነገር በታፈነ ቁጥር እያደር ስለሚገማ የቤተ-ክርስቲያኗ ችግር በግልጽ ታውቆ ብልሽቱ የሚጸዳበት መፍትሄ ካልተፈለገ በስተቀር ታፍኖ መቅረቱ መፍትሄ ያመጣል ብዬ ስለማላምን ጉዳዩን ብዙ ሰው የሚያውቀው ቢሆንም ያላወቀውም አውቆ ለቤተ-ክርስቲያኗ ችግር መፍትሄ ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ለማድረግ ለመጻፍ ችያለሁ እንጂ የቤተ-ክርስቲያኗ ልጅ እንደመሆኔ መጠን የቤተ-ክርስቲያኗ ሐፍረት የእኔ ሐፍረት ሳይሆን ቀርቶ አይደለም ደግሞም ምንም የቤተ-ክርስቲያኗ መሪዎች ቢሆኑም ሰይጣን የነፍሰ ገዳይነት መርዙን በልቦናቸው ያስራጨባቸው ግለሰቦች በድብቅ የፈጸሙት እንጂ የቤተ-ክርስቲያኗ ትምህርትና መመሪያ እስካልሆነ ድረስ ቤተ-ክርስቲያኗ የወደቀችበትን ችግር የሚያሳይ እንጂ የቤተ-ክርስቲያኗ ትምህርትና መመሪያ እንደሆነ ተደርጐ የሚያሳፍር ስላልሆነ ይህንንም በማሰብ ለመግለጥ ደፍሬአለሁ።

ሌላው ደግሞ ሕዝባችን እነዚህን ችግሮች አውቆ ተጽዕኖ በማድረግ ካልተከላከለ በስተቀር አሁንም በምንኩስና በጵጵስና ስም እየተካሄዱ ያሉ ተመሳሳይ ድርጊቶችን ለማቆም ሌላ መፍትሄ አለ ብዬ ስለማምን ነው ሌሎችን እግዚአብሔር ቢፈቅድ ወደፊት በሌላ ዕትም እናያለን



በጵጵስና እየተፈጸመ ያለው ይህ ብቻ አይደለም በዝሙትም በኩል ብዙ ለመስማት የሚዘገንን ነገር ነው የሚሰማው ከባለ ትዳሮችና ጋለሞታዎች ጋር ከሚያደርጉት የዝሙት ድርጊት በተጨማሪ ልጅ አገረድ ለሚያቀርብ ደላላ እስከ ሁለት ሺህ ብር እንደሚከፍሉ ከውስጥ አዋቂዎች የሚወጡ ታማኝ መረጃዎች ያስረዳሉ። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በዝሙት የሚፈጽሙትን ደባ በተመለከተ ወደፊት በሌላ ኅትም በፎቶግራፍ በተደገፈ ማስረጃ አወጣዋለሁ ለቤተ-ክርስቲያን የሚጠቅማት ሆኖ ከተገኘ ብዙዎቹ ከእነ ማዕረግ ልብሳቸው በዝሙት ተግባር ላይ ሲንዘላዘሉ የተገኙበት ማስረጃ ብዙ ነው የግለሰቦችን ኃጢአት መዘርዘር ያን ያህል ጠቃሚ ባይሆንም ይህ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈው እንደተሰጣቸው ስላልኖሩ ነው ጌታችን ሳያገቡ መኖር ለሁሉ የሚቻል አይደለም ብሏል /ማቴ 19:11 እነርሱ ግን ለገንዘብና ለሥልጣን ብለው ባልተሰጣቸው እየኖሩ እንዲህ ሲሆኑ ይኖራሉ። በገንዘብ ዝርፊያ የሚፈጽሙትን የውንብድና ሥራም ወደፊት በሌላ ዕትም የምናየው ይሆናል።ቤተክርስቲያንን የሚጠቅማት መሆኑ ከታመነበት:-

## ምንኩስናን ለማስፋፋት እየተካሄደ ያለ ሴራ

ቤተ-ክርስቲያን በመነኩሴ ብቻ እንድትመራ ለማድረግ በነዚያው በመነኮሳቱ በርካታ ጥረቶች እየተካሄዱ ይገኛሉ ከነዚህ ጥረቶች ጥቂቶችን እንመልከት:-

## የሥልጣን የበላይነትን በመቆጣጠር

ቀደም ሲል እንዳየነው ባለትዳር ጳጳስ አይሆንም ብለው ባለትዳሮች በቤተ-ክርስቲያን ጉዳይ ላይ ወሳኝ ለሆነው የሲኖዶስ አባል እንዳይሆኑ ከልክለዋል የጵጵስና ማዕረጉንስ ይሁን ቤተ-ክርስቲያኗ ልትባርክና ልትቀደስ የምትችለው በመነኩሴ ጳጳስ ብቻ ነው ብለው በማሰብና ባለትዳርም ቅድስና እንደሌለው በማሰብ ይሆናል ያደረጉት በሲኖዶስ ስብሰባ ጊዜ ባለትዳር ምሁራን የሲኖዶሱ /የጉባኤው/ አባል በመሆን በቤተ-ክርስቲያኗ የአስተዳደር ጉዳይ ላይ ሐሳብ በመስጠትና በመወሰን እንዳይሳተፉ መደረጉ ለምን ይሆን ባለትዳሮች የሲኖዶስ አባላት ሆነው የሚሰጡት ሐሳብና ውሳኔ ቤተ-ክርስቲያኗን ያረክሳት ይሆን?

በሲኖዶሱ እንዳይሳተፉ መከልከላቸው ብቻ አይደለም በጳጳሳት የተወሰኑትን ውሳኔዎች ለማስፈጸም ዋና ዋና ቁልፍ የሥልጣን ቦታዎች በነርሱ በጳጳሳቱ የተያዙ ናቸው:: ሁለት ምሳሌዎች ላንሳ ቀደም ሲል ከፓትርያልኩ በመቀጠል በቤተ-ክርስቲያኒቱ ጉዳዮች ላይ የሚያዝዝ የጠቅላይ ቤተ-ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ የሚሾመው ከጳጳሳት አልነበረም ያልመነኮሰም ይሾም ነበር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ያልመነኮሰ ወይም ጳጳስ ያልሆነ እንዴት እኛን ጳጳሳቱን ያዝዘናል በማለት ጳጳስ ያልሆነ የቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ እንዳይሾም ብለው ከልክለዋል ይህ የሥልጣን ክፍል በሲኖዶስ የሚወስነውን የቤተ-ክርስቲያን ጉዳይ ሁሉ የሚያስፈጽም የሥልጣን ክፍል ነው:: የጠቅላይ ቤተ-ክህነት ሠራተኞች በሙሉ የሚሠሩት ከፓትርያርኩ በመቀጠል ከዚህ ቦታ በሚቀመጠው ጳጳስ ትዕዛዝ ብቻ ነው::

የሀገረ ስብከቶችንም ስንመለከት በየወረዳው በየአጥቢያው የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የሚንቀሳቀሱበት በሀገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ ትዕዛዝ ብቻ ነው:: የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅና ሌሎችም ሠራተኞች የጳጳሱ አገልጋዮች እንጂ በቤተ-ክርስቲያን አስተዳደር ጉዳይ ላይ የወሳኝነት ድርሻ የላቸውም ሥራ አስኪያጁ እንኳን ከጳጳሱ ትዕዛዝ ትንሽ ቢያፈነግጥ ጳጳሱ ለጠቅላይ ቤተ-ክህነት አመልክቶ የማስቀየር ወይም ከሥልጣኑ እስከ ማስነሣት መብት አለው ከዚያም በምትኩ ራሱ የመረጠውን ሰው አቅርቦ የማሾም ሥልጣን አለው ያም ፀጥ ለጥ ብሎ ካላገለገለ የዚያኛው እድል ስለሚገጥመው ፀጥ ለጥ ብሎ ይገዛል::

ባጠቃላይ በጠቅላይ ቤተ-ክህነትም ሆነ በየሀገረ ስብከቱ ያሉትን የአስተዳደር ሁኔታዎች ስናይ ጳጳስ ጌታ ያልመነኮሰ የቤተ-ክርስቲያን ሠራተኛ ደግሞ አገልጋይ ሆነው ነው የሚኖሩት ወይም እንደ ፊውዳሉ ሥርዓት ጳጳስ እንደባለ ጉልትና ባለ ርስት ሌላው ሠራተኛ እንደጭሰኛና ገበሬ ሆነው ነው የሚኖሩት በጠቅላይ ቤተ ክህነትም ሆነ በየሀገረ ስብከቱ ያሉ ሠራተኞች ለጳጳስ የሚሰግዱትን ያህል ለኢየሱስ ክርስቶስ አይሰግዱም ውስጣቸው ደስተኛ ባይሆንም እንኳ ለነፍሳቸው ለኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋቸው ለጳጳስ መስገዳቸው አይቀርም ምክንያቱም ካልሰገዱላቸው ጨካኞች ስለሆኑ ከሥራቸው ያባርሯቸውና በርሃብ ይገድሏቸዋል በዚህ ጉዳይ ስንቶቹን ያለበቂ ምክንያት አባረዋቸው በርሃብ እየተሰቃዩ ያሉ ስንቶች ናቸው::



እነዚህን በመሳሰሉት አንድ ጳጳስ በቤተ-ክርስቲያን ያለውን የፊውዳሉ ሥርዓት የፈላጭ ቆራጭነት ሥልጣን በማየት ለእውነተኛው ጽድቅ ሳይሆን ጳጳስ ሆነው ፈላጭ ቆራጭ ለመሆን የሚመነኩሱ ብዙዎች ናቸው እንዲያውም ከሌላው ይልቅ ለዚህ ብለው የሚመነኩሱ ይበዛሉ

ከጵጵስና ማዕረግ በታች ያሉት መነኮሳትም ቢሆኑ ቀሪው የሥልጣን ክፍል በነርሱ እንዲሸፈን እየተደረገ ነው:: ከጵጵስና ማዕረግ በታች ያለው ሌላው የሥልጣን ክፍል አንዱና ዋነኛው የአጥቢያ ቤተ-ክርስቲያን አለቅነት ነው:: ይህ የሥልጣን ክፍል አብዛኛው የተያዘው በመነኮሳት ነው::

በአዲስ አበባ ብቻ ብንመለከት ከዘጠና አምስት በመቶ በላይ የቤተ-ክርስቲያን አለቆች መነኮሳት ናቸው

## በአሸበረቁ የቤተክርስቲያን ሕንፃዎች መነኮሳት ብቻ እንዲቀድሱባቸው ማድረግ

እልቅና ሌላ በአዲስ አበባም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች አንዳንድ ታላላቅ የቤተ-ክርስቲያን ሕንፃዎች ሲሠሩ ባለትዳር ካህናት እየወጡ መነኮሳት ብቻ እንዲቀድሱባቸው እየተደረገ ነው:: መነኮሳት ብቻ እንዲቀድሱ መደረግ የሚገባው ቦታው መነኮሳት የሚኖሩበት ገዳም ቢሆን መልካም ነው::

ጉዳዩ እየተደረገ ያለው ግን እንዲያውም መነኮሳት ሊኖሩበት በማይገባው በከተማ ነው:: ይህ ደግሞ ምንኩስና ገዳማዊ ሥርዓቱን ለቆ አሁን እየታየ ባለው ሁኔታ በሥርዓት አልበኝነት መንገድ እንዲስፋፋ ለማድረግ እየተካሄደ ያለ ሕገ ወጥ ድርጊት ነው ሕገ ወጥ የሚያደርገው አስቀድመን እንዳየነው የቤተ-ክርስቲያኗ የሥርዓት መጽሐፍ የሆነው ፍትሐ ነገሥት መነኮሳት በከተማ እንዳይኖሩ ስለሚከለክል ነው ፍትሐ ነገሥቱ መነኮሳት በከተማ አይኑሩ እያለ (በመንኩሴ ከገዳም ዓሣ ከባሕር ክወጣ አይረባም እንዲሉ) በታላላቅ ከተሞች የሚሠሩ የቤተ-ክርስቲያን ሕንፃዎች ባለትዳር ካህናትን እያስወጡ መነኮሳት ብቻ እንዲቀድሱባቸው ማድረግ ሥርዓት አልበኝነት ነው:: ደግሞ እኮ ሲጠየቁ መነኮሳት ብቻ እንዲቀድሱበት የሚደረገው ቦታው ገዳም ስለሆነ ነው ይላሉ ይህም በራሱ አንድ ስሕተት ነው እንዴት ሆኖ ነው ከተማ መካከል ገዳም ሲሆን የሚችለው ገዳም ማለት እኮ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናየው ሰው የማይደርስበት ምድረ በዳ ማለት ነው በግዕዙ «ወሰደ

መንፈስ ለእግዚእ ኢየሱስ ገዳመ» ያለው በአማርኛ «ጌታ ኢየሱስን መንፈስ ወደምድረ በዳ ወሰደው» ነው የሚለው /ማቴ 4፥1/

«ወበውእቱ መዋዕል በጽሐ ዮሐንስ መጥምቅ እንዘ ይሰብክ በገዳመ ይሁዳ» ያለውንም በአማርኛው «በዚያን ወራት መጥምቁ ዮሐንስ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ» ነው የሚለው /ማቴ 3፥1፡፡

በነዚህ በሁለቱ ጥቅሶች ላይ ስንመለከተው ገዳም የሚለው ቃል ምድረ በዳ ተብሎ ነው የተፈታው በምንኩስና የአኗኗር ታሪክ ስንመለከትም ገዳም ማለት መነኮሳት ብቻ የሚኖሩበት ዓለማዊ ሰው የማይኖርበት ምድረ በዳ ማለት ነው ታዲያ የዛሬዎቹ ከየት አምጥተው ነው መሀል ከተማ ያሸበረቀ ሕንፃ ሠርተው ገዳም ብለው መሰየማቸው ምንኩስናው ከተሜ ከሆነ ዘንድ ገዳሙም ከተሜ ይሁን ተብሎ ይሆን? ምንኩስና ሕገ ወጥ ከሆነ ገዳሙስ ለምን ሕገ ወጥ አይሆንም ብለው ይሆን?

በነዚህ ያሸበረቁ ሕንፃዎች መቅደሶች ውስጥ ባለትዳሮች እንዳይቀድሱ መደረጉ ምናልባት መቅደሱን ያረክሱታል ተብሎ ይሆን? ይህ ደግሞ ጋብቻን እንደርኩሰት መቁጠር ነው፡፡

አስቀድመን እንዳየነው ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ዓይነት ትምህርት የክፉዎች ትምህርት ብሎታል፡፡ /1ጢሞ 4፥1-3/ እናም ይህ ሕገ ወጥና የክፉዎች ትምህርት ምንኩስናን በሕገ ወጥ መንገድ ለማስፋፋት እየተደረጉ ካሉት ሴራዎች አንዱ እንጂ ለጽድቅ ተብሎ የሚፈጸም ድርጊት አይደለም፡፡

## ወደ ውጪ ሀገር መላክ

በድህነታችን ምክንያት ብዙ ኢትዮጵያውያን ከሀገር ውጪ ወጥተው ሠርተው ማግኘት ይፈልጋሉ ስለዚህ በዚህም ምክንያት የተለያየ ዘዴ እየፈለጉ ከሀገራቸው ይወጣሉ በቤተ-ክርስቲያንም እንደዚሁ የተሻለ ገቢ ለማግኘት ወደ ውጪ ሀገር ለመሄድ ተመሳሳይ ሽኩቻ አለ በዚህም ሽኩቻ ምንኩስናን ለማስፋፋት እየተፈጸመ ያለው ሴራ እየተሠራበት ነው በየጊዜው በርካታ መነኮሳት ወደ ውጪ ሀገር ይላካሉ ያልመነኮሱ አገልጋዮች ግን እንዲሄዱ አይፈቀድላቸውም ይህም ሁኔታ ብዙ ድሆች ያለፍላጎታቸው መነኮስን ብለው ቆብ እንዲጭኑ አድርጉአቸዋል፡፡



በእርግጥ ከሀገር ሀገር ተዘዋውሮ ለማስተማር ካገባው ያላገባው ይሻላል ነገር ግን እነዚህ ሰዎች በሀገር ውስጥ እንደምናያቸው አካሄዳቸው ለወንጌል አይደለም ብዙዎቹ ወደ ውጪ ሀገር የሚላኩትን ስናያቸው ቀድሶ ከማቁረብ ያለፈ የወንጌል አገልግሎት ችሎታ ያላቸው አይደሉም ልብሳቸውን በማሳመር ለበላዮቻቸው በመስገድ የመሄዱ ጉዳይ የተሳካላቸው እንጂ በወንጌል አገልግሎት ትጋታቸው የተመሰከረላቸው በትምህርት ብቃታቸው ወንጌልን ለማስተማር የሚችሉ አይደሉም ይህንንም አብዛኛው የቤተ ክህነት ሠራተኛ የሚያውቀው ጉዳይ ነው ሕገ ወጥ ምንኩስና እንዲስፋፋ በሚደረገው ጥረት ላይ ግን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

## የትምህርት እድል ቅድሚያ መስጠት

በሰዋስወብርሃን ቅዱስ ጳውሎስና በቅድስት ሥላሴ ኮሌጆች የሚሰጠውን የትምህርት እድል ቅድሚያ ለመነኮስ በመስጠት በዚህም በኩል ምንኩስናን ለማስፋፋት ጥረት እየተደረገ ነው ይኸውም ከየሀገረ ስብከቶች ወደ ትምህርት ቤቶች ከመላክ ጀምሮ ነው የሚከናወነው ለምሳሌ ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ሀገረ ስብከቶች ተማሪ እንዲልኩ የሚላክ ደብዳቤ ሀገረ ስብከቶች ቅድሚያ ለመነኮሳት እንዲሰጡ ያዝዛል መነኩሴ ከሌለ ነው ያልመነኮሰ የሚላከው በመግቢያ ነጥብም ቢሆን የመነኮሰና ያልመነኮሰ በእኩል ነጥብ አይደለም የሚገቡት ያልመነኮሰው ከሚገባበት ባነሰ ነጥብ መነኩሴው ይገባል ይህ ቤተ-ክርስቲያኗን ለመጥቀም ሳይሆን ምንኩስናን ለማስፋፋት እየተደረገ ያለ ሴራ ነው በእርግጥ አስቀድሜ እንዳልሁት አብዛኛዎቹ የዘመኑ መነኮሳት የሚመነኩሱት ሰነፎች ስለሆኑ ትምህርት እንቢ ሲላቸው ስለሆነ በዝቅተኛ ነጥብ እንዲገቡ ካልተደረገ ያልመነኮሰው በሚገባበት ነጥብ የሚገባ ሳይገኝ ይችላል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቀቀ መነኩሴ መገኘቱም በራሱ አንድ ጥሩ ነገር አይደል ለነገሩ በአንድ በኩል ሲታይ ደግሞ ሳይማሩ ዝም ብለው ከሚያጭበረብሩ ሲማሩ ሊያገናዝቡ ይችሉ ይሆናል፡፡

መማራቸው አይከፋም መንግሥት ለሴቶችና በልማት ኋላቀር ለሆኑ ክልሎች ተማሪዎች በዝቅተኛ ነጥብ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲገቡ አድርጓል፡፡ይህም የሆነው ሴቶች የተለያየ ተጽእኖ ስለሚደርስባቸው ከወንዶች ጋር እኩል የትምህርት ተሳታፊዎች እንዲሆኑና በሁለቱም ጾታዎች

ትምህርቱን ሚዛናዊ ለማድረግ በዚህም ሀገሪቱ እንድታድግ ነው በልማት ኋላቀር የሆኑ ክልሎችም በቂ የተማረ ኃይል በማግኘት ከሌሎቹ ክልሎች ጋር አብረው በልማት ለመራመድ እንዲችሉ ነው::

መነኮሳት በዝቅተኛ ነጥብ እንዲገቡ መደረጉስ ለምንድን ነው? ቢባል ምንኩስና በከተማ እንዲስፋፋ ለማድረግ ነው መነኮሳት እንደሴቶች በዝቅተኛ ነጥብ ይግቡ ሲባል ሴቶችስ በቤት ውስጥ ሥራ በተለያየ የባህል ተጽዕኖዎች በተመቻቸ ሁኔታ ስለማይማሩ እንደ ወንዶች ከፍተኛ ነጥብ ሊያመጡ ስለማይችሉ ነው መነኮሳትስ ካልመነኮሱት ጋር ተወዳድረው የሚያስገባቸው ነጥብ አያመጡም ተብሎ መታሰቡ በምን ምክንያት ነው? መልሱ ይሆናል ብዬ የማስበው ያው አስቀድሜ እንዳልሁት ሰነፎችና አውደልዳዮች ስለሆኑ ተግተው ስለማይማሩ ደህና ነጥብ ሊያመጡ ስለማይችሉ ነው::

ይህንንም እንደነርሱ በማውደልደልና ጊዜያቸውን ያለአግባብ በማሳለፍ በኋላ ቆብ በመጫን በአቋራጭ ሥልጣን ላይ የወጡ መሰሎቻቸው ስለሚያውቁ ችግራቸውን በመረዳት በዝቅተኛ ነጥብ እንዲገቡ ፈቅደውላቸዋል አስቀድሜ እንዳልሁት ይህ ሁኔታ ሳይማሩ ሥልጣን ላይ ከሚወጡ በእንደዚህ ሁኔታ ወደ ትምህርት እንዲመጡ አድርጐ ማስተማሩ ባይከፋም በሌላ መልኩ ደግሞ ጊዜውን በዋዛ በፈዛዛ ያሳለፈ የከተማ ወንበዴ ሁሉ የምንኩስናና የክርስትና ዓላማ ሳይኖረው በዝቅተኛ ነጥብ ለመግባትና የኑሮ አማራጩን ለማመቻቸት ቤተ-ክርስቲያንን የወንበዴዎች መናህሪያ ሊያደርጋት ይችላል የምንኩስና ሥርዓቱ እንዲህ በሥርዓት አልባነት እስከቀጠለ ድረስ ማነኵስኩ ለማለት እንደሆነ ችግር የለም እንደድሮው ሁለት ሦስት ዓመት በአመክሮ ይፈተን አይባል ከፈለገ እሁድ መንኵሶ ሰኞ መግባት ይችላል አመንኳሾቹም በእንደዚህ ዓይነት ምንኩስና እንዲስፋፋ ስለሚፈልጉ ደስታቸው ነው እንኳ ልመንኵስ ብሎ ጠይቆ መንኵስና ወደ መንፈሳዊ ኮሌጅ ላስገባህ ካልመነኮስህ እድሉ አይሰጥህም እያሉ የሚያባብሉ ጳጳሳት ብዙዎች ናቸው::

ሌላው ደግሞ በሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ኮሌጅ ከሚደረገው አንድ ምሳሌ ላንሳ በ1997 ዓ.ም የተፈጸመ ሁኔታ ነው ወደትምህርት ቤቱ ለመግባት በርካታ ትምህርት ፈላጊ ተማሪዎች ለመወዳደር በግቢው ተሰብስበዋል ::



በዚህ ጊዜ የሚፈትኑት ጳጳሳትና ሌሎችም የቦርዱ አባላት ፈተናውን ለመፈተን ከገቡ በኋላ ቅድሚያ ለመነኮሳት በሚለው እቅዳቸው አንዳንድ ሀገረ ስብከቶች የመነኮሰና ያልመነኮሰ እያደረጉ ልከው ስለነበር የሀገረ ስብከቶችን ስም እየጠሩ የመነኮሰውን እየተቀበሉ ያልመነኮሰውን ቦታ የለህም በማለት በፈጸሙት ግፍ ብዙዎቹ የተማሩት የቤተ-ክርስቲያን ልጆች እድሉን እናገኛ ለን ብለው መጥተው በአዲስ አበባ ከተማ ለአንድ ወርና ለአሥራ አምስት ቀናት ከተንገላቱ በኋላ በእንደዚህ ያለ ግፍ ሲከለከሉ እያለቀሱ ሄዱ ብዙዎቹ በእምነታቸው ያልፀኑ ስለነበሩ በብስጭት እምነታቸውን ለወጡ እኔም በወቅቱ ከዚያ ስለነበርኩ የብዙዎች በርሃብ መሰቃየትና በዕለቱ ያነቡት እንባቸው እስከአሁን በውስጤ ስላለ ምንኩስናን ለማስፋፋት እየተፈጸሙ ካሉት ብዙ ግፎች እንደምሳሌ አነሳሁት ይህንን ድርጊት የፈጸሙት በዋናነት በወቅቱ የነበሩት የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ጳጳስ ናቸው::

እንዲያው ለምሳሌ እነዚህን በዋናነት አነሳሁ እንጂ ምንኩስናን ለማስፋፋት እየተፈጸሙ ያሉ ድርጊቶች እነዚህ ብቻ አይደሉም ካልመነኮስህ ሥራ አትቀጠርም፣የትምህርት እድል አታገኝም ብትመነኩስ ግን እድሉ ይሰጥሃል፣ወደ ውጪ ሀገር እልክሃለሁ፣የቤተ-ክርስቲያን አስተዳዳሪ አደርግሃለሁ እያሉ በመስበክና ማባበያ በመስጠት ሃያ ዓመት ያልሞላቸውን ሕፃናት ሳይቀር እያባበሉ የሚያመነኩሱ ጳጳሳት አሉ ይህ ሁሉ ነው እንግዲህ ምንኩስና ፈሩን እንዲለቅ ያደረገው::

እንደዚህ የሚያደርጉት በወንዶችን ብቻ አይደለም ወጣት ሴቶችንም እያታለሉ ገዳም ይገቤሽ ልሂድ እያሉ ለነርሱ በሚመቻቸው ገዳም አሰንብተው መንኩሺ ብለው ቆብ አስጭነው መነኩሴ ናት በሚል ሰበብ እንደ ቅምጥ አድርገው ይዘው የሚኖሩ አሉ::

በነገራችን ላይ አሁን አሁን ሴቶች መነኮሳትም በማታለሉ ሥራ እየተሳተፉ ናቸው:: ለወንዶች መነኮሳት እናንተ ከምትመጡ እኛ እንምጣላችሁ ብለው ነው መሰለኝ ጠቅላይ ቤተ ክህነት አካባቢ ውብ ውብ የሆኑ ሴቶች መነኩሴ ነን እያሉ ቆብ ጭነው ከጳጳሳቱና ከሌሎችም መነኮሳት ሥር ሥር ሲሄዱ ይታያሉ ሆኖም ግን ከዚያው ከወንዶቹ መነኮሳት በመጠጋት ገንዘብ ለማግኘት እንጂ በክህነት ስለማያገለግሉ ምዕመናንን

እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ ለጥያቄዎቼ ቀና መልስ በመስጠት የቤተ-ክርስቲያንን ችግር ለመፍታት ቤተ-ክርስቲያን እንዳስተማረችኝ የበኩሌን አስተዋጽኦ እንዳደርግ እድሉ ቢሰጠኝ ኑሮ እንደዚህ ዓይነት ጽሑፍ መጻፍ ባላስፈለገኝ ነበር ነገር ግን ጩኸቴን የሚሰማና ችግሩን ከማስተካከል ይልቅ የሰዎችን ጥያቄ በሰዎች ላይ የበቀል እርምጃ በመውሰድ መፍታት በሚለው ጸረ ወንጌል በሆነው ከነገሥታቱ ተወርሶ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ሥር ሰዶ በቀረው ፊውዳላዊ አስተሳሰብ በመመራት ጥያቄዎቼን ከመስማት ይልቅ በእኔ ላይ እርምጃ በመውሰድ ጩኸቴን ለማፈን በመመከሩ እንዲህ በይፋ ለመጻፍ ተገድጃለሁ አሁንም ጽሑፌ በዚህ ብቻ ስለማያበቃ ሌሎች ጽሑፎችን ከማውጣቴ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለሲኖዶሱ አቀርባለሁ ጥቄዎቼን ሰምቶ ተገቢውን መልስ የሚሰጠኝ ከሆነ እንደዚህ ያሉ ጽሑፍ መጻፍ የቤተ-ክርስቲያኗን ችግር ይፈታል ብየ አላምንም

## ጥያቄዎች

### ጥያቄ ክፍል አንድ:-

1.1 አስቀድሜ በዚች መጽሐፍ ከዘረዘርኋቸው ስለምንኩስና ከሚናገሩ የሥርዓት መጻሕፍትና ከመጽሐፍ ቅዱስ አንፃር ሌላው ቀርቶ ከቃለ አዋዲሁ ጭምር አንፃር ሲታይ አሁን እየተፈጸመ ያለው የምንኩስና ሁለንተናዊ ሁኔታ ልክ ነው ወይ ልክ ካልሆነስ ሲኖዶሱ የማያስተካክልበት ምክንያት ምንድን ነው?

1.2 በዚች መጽሐፍ የዘረዘሩት የምንኩስና ችግር ሁሉ ውሸት ከሆነ ማስተባበያ ስጡ እውነት ከሆነ ደግሞ አስተካክሉ መልሱ ለእኔ ሳይሆን ለምትመሩት ሕዝብ ነው::

### ጥያቄ ክፍል ሁለት :-

2.1 ጳጳስ መሾም ያለበት መነኩሴ ብቻ ነው እንጂ ባለትዳር መሾም አይገባውም መባሉስ አስቀድሜ እንደዘረዘርሁት በመጽሐፍ ቅዱስና በፍትሐ ነገሥት ስለ ጳጳስ ሹመት ከተደነገገው አንፃር ልክ ነው? ልክ ነው ከተባለስ መጽሐፍ ቅዱስና ፍትሐ ነገሥት ተሳስተዋል ማለት ነው?



ይህ ሁኔታስ ቤተ-ክርስቲያኗን ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ውጪ የምትመራ አያስብላትምን?

2.2 ጳጳስ ባይሆኑም እንኳን የቤተ-ክርስቲያን ምሑራን በቤተ-ክርስቲያኗ ሁለንተናዊ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሲኖዶስ አባል የማይሆኑበት ምክንያት ምንድን ነው? 2.3 ቀደም ሲል የጠቅላይ ቤተክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ካልመነኮሱትም ይሾም ነበር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ይህ ሁኔታ ተከልክሎ ጳጳስ ብቻ እንዲሾም ተደርጓል ይህ ሁኔታ ቤተ-ክርስቲያኗ በመነኩሴ ይልቁንም በጳጳሳት ብቻ እንድትመራ የጳጳሳትን የሥልጣን ሽሚያ የሚያሳይ ሁኔታ አይደለም ወይ ባለትዳር ቢሾምስ ችግሩ ምንድን ነው?

### ጥያቄ ክፍል ሦስት:-

**3.1** በ1957 ዓ.ም በዓፄ ኃይለ ሥላሴ ጋባዥነት ቤተ-ክርስቲያናችን ለሀገራችን አዲስ አበባ ውስጥ አዘጋጅታው በነበረው የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባዔ ላይ ጉባዔው ቤተ-ክርስቲያን ከዘመኑ ጋር አብራ መራመድ እንድትችል ሥርዓትና አስተዳደሯን ማሻሻል እንዳለባት ወስኗል::

ለምሳሌ:- የዓቢይ ጾም ቀናት መቀነስ እንዳለባቸው የቅዳሴውም ቅዳሴው ምሥጢሩን እንደጠበቀ ሰዓቱ መቀነስ እንዳለበት ጉባኤው ወስኗል በዚህም መሠረት ለአሁኑ ሲኖዶስ የማቀርበው ጥያቄ በአሁኑ ሰዓት ቤተ-ክርስቲያንና የአስተዳደር መዋቅር ከዘመኑ ጋር አብሮ በሚሄድ መልኩ መሻሻል የለበትም ወይ?

**3.2** በመጨረሻም የማቀርበው ጥያቄ በርካታ የቤተክርስቲያኒቱ ልጆች ቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ችግሮች አሉ ይስተካከሉ ብለው በመናገራቸው ብቻ እንደ ስህተተኞች ተቆጥረው በጉባኤ ቀርበው ሳይጠየቁ ሐሳባቸው እየታፈነ በተለያየ ምክንያት ከቤተክርስቲያን ተባረው አሁንም በያሉበት ቦታ ሆነው ድምፃቸውን በማሰማት ይገኛሉ ስለዚህ ቤተክርስቲያኗ የእነዚህን ልጆቿ ጩኸት ለማፈን እያደረች ልቧን ከማጠንከር ይልቅ

በጉባኤ አቅርባ ሀሳባቸው ትክክል ከሆነ መቀበል ስህተተኞች ከሆኑ ደግሞ ስህተተኞች ናቸው ብላ በጉባኤ ማሳወቅ አይገባትም ወይ? ይህ ካልሆነና ቤተክርስቲያኗ መፍትሄ ካልፈለገች ወደእማያባራ ውድቀትና ውርደት እያመራች መሆኑ በግልጽ እየታየ ነው ሲኖዶሱ ይህንን እንዴት ያየዋል? በተረፈ መልካም መልስ በመስጠት ፋንታ በአጸፋው የበቀል እርምጃ መውሰድ ከአሁን በፊትም ቤተ-ክርስቲያኗን አልጠቀማትም በታሪክ እንደሚታወቀው አሁንም እየተደረገ እንዳለው ይህች ቤተ-ክርስቲያን ስንቶቹን አሳዳለች ለአብነትም እንደነ ኪዳነወልድ ክፍሌ የመሳሰሉ ሊቃውንትን ስታሳድድ መኖሯን መጥቀሱ ይበቃል:: ይህን በማድረጓ ተጠቅማለች ወይ የሚለው ደግሞ ብዙኃኑ የሚጠይቀው ጥያቄ ነው እኔ በበኩሌ የተጠቀመች አይመስለኝም እንኳን አሁን በሰለጠነው ዓለም በድሮው በፊውዳሉ ሥርዓትም ይህ ዓይነት ድርጊት ሀገሪቱንም ቤተ-ክርስቲያኗንም አልጠቀማትም::

የቤተክርስቲያን ሁለንተናዊ ችግር በማለቅ ላይ ባለው ሁለተኛ ሺህ ዓመት አብሮ አብቅቶ በመጪው ዓመት በምንጀምረው ሦስተኛ ሺ ዓመት ቤተክርስቲያናችን የተሻለ ጉዞ እንደትጓዝ ከእያንዳንዳችን ልጆቿ ችግሮቿን የመቅረፍ ተነሳሽነት ያስፈልጋል::

ስለሺህ ዓመት (ሚሊኒየም) ካነሳሁ በዚህ አጋጣሚ ለሺህ ዓመቱ ማስታወሻ በአንዲት የአማርኛ ቅኔ ጽሑፌን ላጠቃል

ፀቅርስ በታሪክ ፈረንጅ አይበልጠንም
ካላጠና በቀር የእኛን ቀን አያውቅም::

ሕብረ ቃል የእኛን ቀን አያውቅም
ሰም የእኛን የቀን አቆጣጠር አያውቅም::

ወርቅ የእኛን «ቀ» ን ፊደል አያውቅም ወይም በእንግሊዘኛው ፊደል «ቀ» የለችም ማለት ነው::



# ዋቢ መረጃዎች

- መጽሐፍ ቅዱስ
- ፍትሐ ነገስት
- ደቂቀ እስጢፋኖስ
  /በሕግ አምላክ/
  በፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ከግዕዝ ወደ አማርኛ የተተረጐመ
- ሃይማኖተ አበው
- ሦስቱ መጻህፍተ መነኮሳት
- ፊልክስዩስ
- ማር ይስሐቅ
- አረጋዊ መንፈሳዊ
- ከተለያዩ ግለሰቦች የተሰባሰቡ የጽሁፍ የድምጽና የምስል መረጃዎች
- የአማርኛ የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት
  ከዶክተር ሰርግው ሀብተ ስላሴ
  በምዕራብ ጀርመን ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት
  ከሚማሩ ኢትዮጵያውያን የተዘጋጀ ሃድልበርግ 1989
- አንድ እረኛ ለአንድ መንጋ በአለማየሁ ሞገስ